# የታወቀ የእግዚአብሔር አውራው ሰራ

በጣም፡ አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ። ከሶስት ወራት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መድረክ መውጣቴ መሆኑን እንድናገር፡ ቢሊ ፈልጎኛል። እርሱ... ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲመሰክር፡ ወደዚህ ሳወጣው፡ "በመጀመሪያ ደረጃ፡ ፈርቻለሁ" እንዳለ፡ አስታውሳለሁ። እኔም፡ እንዲሁ ነኝ። በአገልግሎት ውስጥ ወደ ሰላሳ-አምስት ዓመታት ገደማ አሳልፌያለሁ፡ ይህ ደግሞ በአገልግሎት ከቆየሁበት ጊዜ ጀምሮ ከመድረክ ርቄ የቆየሁበት ረጅሙ ጊዜ ነው። ጥቂት እረፍት አስፈልጎኝ ነበር፡ ስለዚህ እኔና ወንድም ሞዝሊ፡ እንዲሁም እዚህ ካሉት አንዳንድ ወንድሞች ጋር፡ ለአደን ጉዞ ወጥተን ነበር። አሁንም በደንብ አርፈናል። ይህ ደግሞ ከመሰከረም መጀመሪያ ገደማ ጀምሮ... የመጀመሪያ ስብሰባዬ ነው። ደግሞም የሆነ ነገር ነው... አገልግሎት ማለት አብራችሁት ልትዘልቁ የሚገባችሁ ነገር ነው።

2 አሁንም የአየር ማቀዝቀዣውን እንዲያጠፉት፡ ወይም ማጥፋት ይችሉ እንደሆነ ጠይቄያቸዋለሁ፡ ምክንያቱም ለመስማት እንደሚያስቸግር አውቃለሁ። አንድ ሰው ምስክርነቱን ሲሰጥ፡ ከባድ ነው፡ አውቃለሁ። እነርሱን መስማት ለእኔም ከብዶኝ ነበርና። አሁን በደንብ ይሰማችኋል? ጥሩ። ያንን እስኪያስተካክሉት ድረስ ወደዚህ ማይክሮፎን ጠጋ ብዬ መቆም እንዳለብኝ አውቃለሁ።

3 ይህ በእርግጥ ለእኔ—ትልቅ ዕድል ነው፡ ስለ ሊቀ መንበሩም—በእውነት አመሰግናለሁ፡ እንዲሁም እዚህ ዩማ ስለሚገኘው የሙሉ ወንጌል ነጋዴዎች ማህበር ቅርንጫፍ፡ እና ስለ መጋቢዎቹ ሁሉ በእውነት አመሰግናለሁ። ከጥቂት ጊዜያት በፊት፡ እዚህ መድረክ ላይ የነበሩትን እነዚህን ድንቅ ዘማሪዎች፡ በስብሰባው ላይ—በስብሰባው ላይ መስማት እፈልጋለሁ። በእውነት በጣም ጥሩ ነበር። ሲዘምሩ፡ ጆን አይቶኝ ይሆን፡ ብዬ—ብዬ ሳስብ ነበር። እንዳየኝም ተስፋ አደርጋለሁ። ስለዚህ፡ ደግሞ፡ ሪቫይቫል ውስጥ እንዳላችሁ ሰምቻለሁ። ወንድምና እህት፡ ስታገለግሉ፡ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ። ፊኒክስና በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኙ ጓደኞቼ ሁሉ፡ ያ... እንዲሁም ካሊፎርኒያ ለሚገኙት ጭምር።

4 ስለ ማህበሩ ቅርንጫፎች አንድ ቃል መናገር እፈልጋለሁ። ወደ ጴንጤቆስጤ ሰዎች በመጣሁ ጊዜ፡ ያኔ... የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን መኖሯን ሳላውቅ፡ የጴንጤቆስጤ ልምምድ አገኘኹ። በዚያን ጊዜ የባፕቲስት ሚሲዮናዊ ነበርኩ። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አስቀድሜ ተቀብዬ ነበርና፡ የተቀበልኩትን ያንኑ ነገር የሚያምኑ አንዳንድ ሰዎች እንዳሉም ተረዳሁ። እነርሱ ደግሞ እኔ ከማግኘቴ ከአርባ ዓመታት በፊት ተቀብለውት ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ እንዳለው፡ ከእርሱ ጋር እኩል ለማድረግ ፈልጌ ሳይሆን፡ ነገር ግን፡ "ያለ ጊዜው እንደተወለደ፡" ዓይነት ሰው እንደሆንኩ አምናለሁ። ነገር ግን... ወንድሞቼ፡ እኛ እንደምንለው ወደ ጥልቁ ገብቼ፡ የጠፋሁ መስሏቸው ነበር።

ዳሩ ግን አንድ ነገር እንደተቀበልኩ እኔ—እኔ አውቅ ነበር። ከዚያም፡ የእኔ ልምምድ ልክ እነሱ እዚያ እንዲጋጠማቸው ዓይነት ነበር። እኔም ያንን መንገድ ነው የምወደው።

5 ሆኖም፡ ወደ እነርሱ ሰመጣ፡ በጣም—ልብ-የሚሰብረው ነገር፡ እነርሱም ልክ እንደ ባፕቲሰት ቤተክርሰቲያናችን፡ በተለያዩ የሐይማኖት ተቋማት፡ ተከፋፍለው እንዳሉ ተረዳሁ። እነርሱም... ጴንጤቆሰጤ የሚባል አንድ ብቻ እንዳለና፡ ሌላ እንደሌለ አሰቤ ነበር። ዳሩ ግን፡ ሰንመረምር፡ በርካታ የተለያዩ የሐይማኖት ተቋማት እንዳሏቸው ደርሰንበታል። ሰለዚህ፡ እ... ሁሉም ጥሩ ነበሩ። በሕይወቴ፡ ካገኘኋቸው፡ እጅግ ምርጥ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ በእነዚህ ቡድኖች ውሰጥ እንደነበሩ አውቃለሁ። እነርሱም—እነርሱም፡ በእርግጥ፡ የተለያዩ የሐይማኖት ተቋማት ነበሩ። የእኔ—የእኔ ሐሳብ ከክርሰቶሰ ጋር፡ በአንድ ልብ መሆን አለብን የሚል ነበር፡ ሰለዚህም ከእነርሱ መካከል የትኛውንም የሐይማኖት ተቋም አልተቀላቀልኩም። በመካከላቸው ቆሜ፡ የሁለቱንም እጆች፡ የሁሉንም እጆች ለመያዝ እየሞከርኩ፡ "እኛ ወንድማማቾች ነን፡" እል ነበር። እኛ እንግዲህ... አንዳችን ከሌላው፡ ጥቃቅን ነገሮች በተለያየ አሰተያየት ማየት የምንችል ነን። ከዚያ ሁሉ በላይ፡ ግን፡ አሁንም ወንድማማቾች ነን፡ ምክንያቱም ከአንድ መንፈሰ ተወልደናል። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነን።

6 ከዚያም የክርሰቲያን ቢዝነሰ ሜን፡ የፋል ጎሰፔል ቢዝነሰ ሜን፡ ይሄኛው ቅርንጫፍ፡ በመጀመሪያው ሰብሰባ ከወንድም ሻካሪያን ጋር ነበርኩ። ድርጅቱ፡ ወይም መዋቅሩ ከመቋቋሙ በፊት እርሱን አውቀው ነበር። ታላቅ ነገር እንደሆነ አሰቤ ነበር። ከእነዚህ የፋል ጎሰፕል ቢዝነሰ ሜን ጋር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመጓዝ፡ ለእኔ የተከፈተ በር ሆኖልኛል።

7 እንግዲህ፡ አንዳንድ ጊዜ፡ አንድ የመጋቢዎች ቡድን ሰታገኙ፡ አንዳንዴ፡ አንድ ሰው አንድ ነገር ሰለተናገረ ብቻ፡ በሌላው ቡድን ላይ ትንሽ ቅሬታ ያድርባቸዋል። በሁሉም ቦታ አይደለም፡ ነገር ግን በየአጥቢያዎች ይገጥሙናል። ለምሳሌ፡ አንደኛው ቤተክርሰቲያን ድጋፍ የሚያደርግ ከሆነ፡ ሌላኛው ከጉዳዩ ጋር ምንም ግንኙነት አይኖረውም።

8 ከፋል ጎሰፕል ቢዝነሰ ሜን ጋር ግን፡ ለእኔ የተከፈተ በር ሆኖልኛል። እነርሱ ያሉበት ሲሆን፡ ወንድሞቼን ሁሉ በአንድ ላይ እሰበሰባለሁ፡ ከዚያም ኅ—ኅብረት ማድረግ እንችላለን፥ ምናልባት ሁለት ፓሰተሮች ሰሜት፡ ወይም የሆነ ነገር አድሮባቸው ሊሆን ይችላል። ይህ ታላቅ የተከፈተ በር ሆኖ ቆይቷል፡ በእነርሱ አጥቢያዎች ውሰጥ እየተናገርኩ፡ አሁን ለዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጉዤላቸዋለሁ።

9 እና እ... ዩማ ምንም እንኳ እኔ ከመጣሁበት፡ ከጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና በጣም እንደምትበልጥ ብገምትም፡ በጣም ትልቅ ከተማ አይደለችም። ሆኖም ሊቀ መንበራችሁን እዚህ አገኛቼዋለሁ። የ... እርሱ... እንዲሁም የቅርንጫፋችሁን የተለያዩ ሰዎች። እዚህም ድንቅ ዕድል ያገኛችሁ ይመሰለኛል።

10 ዛሬ ማታ፡ እዚህ ቁጭ ብዬ ህዝቡን ሳየው፡ እያሰብኩ ነበር። ታውቃላችሁ፡ ይህን ዕድል በቅርቡ እናጣዋለን። የዓለም አብያተ ክርሰቲያናት ካውንሰል በቅርቡ ይውጠናል። የዛሬው አብዛኛው ታዳሚዬ ከጴንጤቆሰጤዎች፡

ከባፕቲስቶች፡ እና—እና ከእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን፡ እንዲሁም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ውጭ ከሆኑት ሌሎች የተዋቀረ እንደሆነ እገምታለሁ። እነርሱም—እነርሱም፡ ትኩረታቸው በዚሁ ላይ ነው፡ መጽሐፍ ቅዱስም ያደርጉታል ያለው ይሄንኑ ነው። ስለዚህ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል፡ በመሆኑም ከእርሱ እንራቅ። ስለዚህ ዛሬ ማታ፡ በመዝሙሩ ላይ፡ ስለ ጌታ መምጣት መቃረብ እንደተነገረው፡ ከምናስበው በላይ ቅርብ ሊሆን ይችላል።

11 በእንደዚህ ዓይነት ኅብረት አንድ ላይ ስንሰበሰብ፡ በውስጣችን የሆነ ነገር እንደሚያደርግ አምናለሁ፡ ይህም እርስ በርሳችን ይበልጥ ያቀራርበናል። እርስ በርሳችን ይበልጥ ስንቀራረብም፡ ወደ እግዚአብሔርም ይበልጥ እንቀራረባለን፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏልና፡ "ከእነዚህ ከሁሉ ለሚያንሱት ከታናናሾች ለአንዱ ያደረጋችሁት፡ ለእኔ አደረጋችሁት።"

12 የት እንደሆነ ባላውቅም፡ ጆሴፍ የሚባል ትንሹ ልጄ፡ በዚህ አካባቢ እንዳለ አስባለሁ። ቢሊም እዚህ ተቀምጧል። ሁለቱ ሴቶች ልጆቼ ወደዚያ ኋላ ተቀምጠዋል፡ ባለቤቴም ጭምር። አሁን ማናችሁም ሰው… የሆነ መልካም ነገር ማድረግ ቢፈልግ፡ ለእኔ ከምታደርጉልኝ ይልቅ ለልጆቼ ብታደርጉላቸው እመርጣለሁ። ስለዚህ እንደ ወላጅ፡ እንደዚያ ይሰማኛል፡ እርሱ ደግሞ የወላጅነት ሁሉ ምንጭ ስለሆነ፡ እግዚአብሔርም የሚሰማው እንደዚሁ ይመስለኛል። እኛ ማድረግ የሚገባን… እርስ በርሳችን ስናገለግል እርሱን ማገልገላችን ነው። እግዚአብሔርን የምናገለግለው በዚህ መንገድ ነው።

13 እናም ይህ እውነት መሆኑን በማወቅ፡ ይሄኛው ቅርንጫፍ በተሰበሰበ ቁጥር፡ በወንጌላውያን-መካከለኛነት የቆመ ስለሆነ… የፉል ጎስፕል ቢዝነስ ሜን የቆመለት የተለየ ዶክትሪን የለውም። እነርሱ የቆሙለት ለሙሉው ወንጌል ብቻ ነው። አንድ ሰው የተለየ አመለካከት ቢኖረውም፡ ያ ምንም ችግር የለውም። ምንም ችግር የለውም። ያም ሆነ ይህ፡ ኅብረት አለን። ስለዚህ እንደዚህ ይሆናል ብዬ አስባለሁ… በዚህች ከተማ የምኖር ብሆን ኖሮ፡ ያ የኅብረቱ ቅርንጫፍ፡ በሚሰበሰብበት ጊዜ፡ ምንም ዓይነት መንገድ ቢኖር፡ እዚያ እገኝ ነበር ማግኘት የምችለውንም ሰው ሁሉ ወደዚያ አመጣው ነበር። ትክክል ነው፡ ምክንያቱም ይህ—ይህ እኛን በአንድ ላይ የሚያጠነክረን ነገር ስለሆነ ነው።

14 ቱሰን ውስጥ ነው የምኖረው፡ እና በዚያ ላለው ቅርንጫፍ፡ ሁልጊዜ እናገራለሁ። ፊኒክስ ውስጥም፡ ወደ አሪዞና ከተዛወርኩ ጀምሮ፡ ጊዜ ባገኘሁ ቁጥር ወደ ፊኒክስ—ወደ ፊኒክስ እመጣለሁ፡ ምክንያቱም… አብሮኝ ሰው ለማምጣት እሞክራለሁ፡ ሰዎችን እጋብዛለሁ፡ ሌሎች አገልጋዮችንም አመጣለሁ።

እንዲህም ይላሉ፡ "እሺ፡ እሺ፡ አየህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ እኛ እንኳን… "

15 እንዲህ እላቸዋለሁ፡ "እናንተ ምንም ብትሆኑ ለውጥ የለውም… ብቻ አብራችሁኝ ሂዱ። እንደ—እንደ ጓደኛ፡ አብራችሁኝ ሂዱ።"

16 ለጥቂት ጊዜ ብቻ ወደዚያው ይዣቸው መሄድ ነው። ማድረግ ያለባችሁ ይህንኑ ብቻ ነው። የያንዳንዱ ሰው ልብ ለኅብረት የተራበ መሆኑን፡ ደርሰንበታል። እኛም ማድረግ ያለብን እንደዚሁ ነው። ይህ ታላቅ የመጨረሻ-ዘመን ምልክት ነው። እግዚአብሔር ይህንን ቅርንጫፍ ይባርክ። ጌታ ኢየሱስ በክብር ወደ ላይ ሊቀበለን እስኪመጣ ድረስ እ—እንዲኖር፡ ጸሎቴ ነው።

17 አሁን፡ በዩማ በኩል ያደረግሁትን የመጀመሪያ ጉዞዬን አስታውሳለሁ። በሰዓት ሠላሳ ማይል ሊጓዝ በሚችል ሞዴል-ቲ ፎርድ ውስጥ ነበርኩ። ዛሬ እየነዳሁ ስመጣ ሳሰበው ነበር። አሁንም ለፎርድ ታማኝ ነኝ፥ አሁንም አንድ አለችኝ፡ ከእርሷ ሌላ ምንም የለኝም። ሆኖም... አሁን፡ ፎርድ መኪናዎችን አልሸጥም። አሁን፡ ይህ ማስታወቂያ መስራቴ አይደለም። አያችሁ? ዳሩ ግን ያ ፎርድ እንዴት እንደነበር አስታውሳለሁ... በእኔ ዕድሜ አካባቢ ያላችሁ ብዙዎቻችሁ ወንድሞች ያንን የቀድሞ ሞደል-ቲ ታስታውሳላችሁ። ይህ በ1927 ነበር። በትኩረት ካልተመለከታችሁ በስተቀር ስታልፉ ዩማን አታገኟትም ነበር። በጣም ትንሽ ነበረች፡ አሁን ግን በእርግጥም አድጋለች። ነገር ግን፡ በፎርድ መኪናዬ በሰዓት ሠላሳ ማይል የምጓዝበት መንገድ፡ አሥራ አምስት ማይል **በዚህ** በኩል፡ አሥራ አምስት ማይል ደግሞ **በዚህ**-በኩል እየከነፈች ነበር። ስለዚህ፡ በአንድ ላይ ስታደርጉት፡ ከመንገራገጩ ጋር እና ከሌላው ጋር ተደምሮ በሰዓት ሠላሳ ማይል ነበረኝ። ዩማ አድጋለች።

18 ይህች ክብርት ቤተክርስቲያን፡ ማለትም፡ ለዚህች ድንቅ እምነት እ— እየተጋደልን ነው።

19 ያንን ላደረግኸው ሁሉ፡ አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ።

20 እርሷም፡ አድጋለች፡ ለዚህም ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው። ጌታ ሁላችሁንም ይባርክ።

21 በእነዚህ ስብሰባዎች አካባቢ፡ ቅርብ ከሆናችሁ፡ እንደምትገኙ፡ ተስፋ እናደርጋለን... በሚቀጥለው እሑድ፡ ፊኒክስ በሚገኘው የማኅበሩ— ቅርንጫፍ፡ እናገራለሁ። ቀጥሎ ባለው እሑድ ደግሞ በፍላግስታፍ እሆናለሁ። ቀጥሎ ባለው ሰኞ፡ በሃያ-አንደኛው ቀን፡ ቱሰን ውስጥ የራት ግብዣ አለ። ሁላችሁም ተጋብዛችኋል።

22 ጌታ ቢፈቅድ፡ ዌስትዋርድ ሆ ሆቴል፡ አዳራሽ ውስጥ የምናገር፡ ይመስለኛል። የሚጀምረው በየትኛው ምሽት ነው? [አንድ ሰው፡ "እሑድ ከሰዓት፡ በዐሥራ ሰባተኛው ቀን ነው" አለ።—አርታዒ።] እሑድ ከሰዓት፡ በአሥራ ሰባተኛው ቀን፡ አነስተኛ የወንጌል አገልግሎት ይኖራል። እነዚህ ዘማሪዎች ያኔ አካባቢ ተገኝተው፡ እንዲያግዙን፡ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚያም እስከ ረቡዕ ድረስ እዚያው እንቆያለን። እሑድ ከሰዓት ይመስለኛል። ያንንም የምናደርግበት ምክንያት የቤተክርስቲያናትን መርሃ ግብሮች ላለማስተጓጎል ነው። ከዚያም፡ ሰኞ ማክሰኞ፡ ከዚያም ረቡዕ በራ-... በዌስት-... በራማዳ ኢንን፡ ራማዳ ኢንን እንሆናለን። ስለዚህ ሐሙስ በዌስትዋርድ ሆ እንጀምራለን። ልክ ነው?

23 [አንድ ወንድም፡ "በዌስትዋርድ ሆ እሑድ፡ ሰኞ፡ ማክሰኞ፡ እንሆናለን። ከዚያም ረቡዕ፡ ወደ ራማዳ ኢንን እንሄዳለን፡ ኮንቬንሽኑ እስኪያልቅም እዚያው እንቆያለን።"—አርታዒ።] ኮንቬንሽኑ የሚያልቀው፡ በራማዳ ኢንን ነው። ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ ብትመጡ ደስ ይለናል።

24 አሁን፡ ወደዚህ መጽሐፍ ከመግባታችን በፊት፡ አንገታችንን ዝቅ አድርገን ደራሲውን እናነጋግር።

25 አሁንም፡ እግዚአብሔር እኛን ወደወሰደበት አፈር ራሳችንን ዝቅ እንዳደረግን፡ ኢየሱስም ከዘገየ፡ አንድ ቀን፡ ወደዚያው መመለሳችን አይቀርም።

እዚህ ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ፡ ከምሥራቅ አንድ መልእክት ደረሰኝ፡ የማውቃት አንዲት ትንሽ እመቤት... ኤዲዝ ራይት የምትባል ትንሽ ልጅ ነበረች። ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ በዘጠኝ ሰዓት፡ እግዚአብሔርን ለመገናኘት አልፋለች። እኛም ወደዚያው መመለሳችን አይቀርም። በጸሎት መታሰብ የሚፈልግ ማንም ሰው እዚህ ካለ፡ እባካችሁ እጃችሁን ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርጉ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

26 የሰማይ አባት ሆይ፡ በዚህ ያማረ ኅብረት፡ መዝሙር እየተደሰትን ሰናልፍ፡ ኦህ፡ ያንን መዝሙር ሰሰማ ልቤን እንዴት እንዳሰፈነደቀው፡ **ዲ ድ ጀን ሲ ሚ**? አባት ሆይ፡ ሁላችንም እያንዳንዳችን፡ እዚያ እንደምንገኝ እምናለሁ። አሁንም ወደ አፈር እኅንብሰናል፡ እ—እ ምስጋናችን—ነሰሐችንን፡ እርሰ በእርሳችን የምናደርገውንም ጸሎት፡ እንድትቀበል እንጸልያለን።

27 አሁንም ወደ ቃልህ ዘወር እንላለን፡ ይኸውም ከሌላው የፕሮግራሙ ክፍሎች—ይልቅ እጅግ የተቀደሰ ወደሚመሰለው የሰብሰባው ክፍል ነው፡ ምክንያቱም በዚህ ሰዓት ከሰዎች ጋር እየተነጋገርን እንደሆነ፡ ወደ እውነት፡ ወደ ክርሰቶሰ፡ ክርሰቶሰ ወደ ሆነው ቃል ልንመራቸው እንደሆነ እናውቃለን። ቃልህንም እንድትከፍትልን እንጸልያለን። እ—እኛ ኀደሎዎች ነን፡ ጌታ ሆይ፡ ዳሩ ግን አንተ ሁሉን ቻይ ነህ። ሰለዚህ ደካማ ጥረቶቻችንን እንድትባርክ እጸልያለሁ፡ ዛሬ ማታም በእግዚአብሔር ቃል ውሰጥ ራሳችንን ሰፍራችንንም እንድናገኝ። አባት ሆይ፡ ይህን ይሁንልን። ምሰጋናንም ለአንተ እናቀርባለን፡ በኢየሱሰ ሰም እንለምናለንና። አሜን።

28 አሁን፡ እዚህ መገኘት በእውነት ደሰ ይላል። ለጥቂት ደቂቃዎች እመለከታቸዋለሁ ብዬ ያሰብኳቸው፡ ጥቂት ማሰታወሻዎች አሉኝ፡ ይህንን አዳራሽ በምሽቱ ረዘም ላለ ጊዜ እንድንይዝ እንደማይፈቀድልን እገምታለሁና። በጴንጤቆሰጤ ህዝብ መካከል፡ ሰሆንም፡ ታውቃላችሁ፡ በመጠኑ፡ እንቀራፈፋለሁ።

29 እሰታውሳለሁ። ምናልባት፡ ነግሬያችሁ ይሆናል። የመጀመሪያውን የጴንጤቆሰጤ አገልጋይ ያየሁት፡ ከሴንት ሉዊሰ የመጡት ቄሰ ሮበርት ዳውገርቲ ነበሩ። ከእናንተ ውሰጥ እሳቸውን የሚያውቅ ይኖራል ብዬ አላሰብም። በመጽሐፉ ውሰጥ የትንሿን ሴት ልጃቸውን ምሰክርነት አይታችኋል። እሱ—እሱ... እርሷ ተሰፋ ከተቆረጠባት በኋላ፡ ከሴንት ቫይተሰ ዳንሰ በሽታ ተፈውሳ ነበር። የመጀመሪያዎቹን የጴንጤቆሰጤ ሰዎችን ያገኘኋቸውም በዚህ መንገድ ነበር።

30 እናም፡ እርሱ ሲሰብክ ለመሰማት፡ ሄድኩ፡ እ—እና፡ እቤት፡ መሰበክ—ይችል ነበር። እሱ... ለምንም ነገር እንኳ አይጠብቅም ነበር። ትንፋሹ እሰከሚያልቅ፡ ፊቱም እሰኪጠቁር፡ ጉልበቶቹም ተጣጥፈው፡ ወለሉንም ሊመታ እሰኪቃረብ ድረሰ ይሰብክ ነበር። ትንፋሹንም ሲሰበሰብ፡ እዚያ ታች እሰከ ከተማዋ መጨረሻ ድረሰ ሊሰማ በሚችል ድምጽ፡ ዳግም፡ ወደ መሰበክ ይመለሰ ነበር። በልቤም፡ "ማይ፡ እኔ—እኔ እንደዚያ በፍጥነት ማሰብ አልችልም።"

31 ጊዜ መውሰድ ይኖርብኛል። በመጠኑም ቢሆን ቀርፈፍ እላለሁ፡ እንዲሁም፡ እያረጀሁም ነው፡ ታውቃላችሁ፡ እያዘገምኩ ነው፡ ሰለዚህ ለጥቂት

ደቂቃዎች እንደምትታገሱኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

32 እንደማይወድቅ የማውቀው፡ አንድ እርግጠኛ ነገር አለ፡ እርሱም ቃሉ ነው። “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ነገር ግን ቃሉ ከቶ አያልፍም።” ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ካላችሁ፡ ከእርሱም ለማንበብ ከወደዳችሁ፡ ወደ ኢሳይያስ መጽሐፍ፡ ኢሳይያስ 53ኛው ምዕራፍ፡ እንገልጣለን። ይህንንም ማንበብ የምፈልገው፡ ለአጭር ጊዜ፡ ዐውደ ጽሑፍን የምንገነባበትን ኃይለ ቃል ለማግኘት ነው።

**የሰማነውን ነገር ማን አምኖ**አል?... **የእግዚአብሔርንስ ክንድ ለማን ተገልጦአል**?

**በፊቱ እንደ ቡቃያ፡ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጎአል፥ መልክና ውበት የለ**ው**ም፥ ባየነውም ጊዜ እንወደው ዘንድ፡ ደም ግባት የለውም።**

**የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥** የሕዘን **ሰው፡... ደዌንም የሚያውቅ ነው፥ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት፥ የተናቀ ነው፡ እኛም አላከበርነውም።**

**በእውነት ደዌያችንን** ተቀበለ፡ **ሕዘናችንንም ተሸከመ፥ እኛ ግን እንደ ተመታ፡ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ፡ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።**

**እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ ስለ** በደላችንም **ደቀቀ፥ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር፥... በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን።**

**እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፥ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ እዘነበለ፥ እግዚአብሔርም... የሁላችንን በደል** በእርሱ ላይ **አኖረ።**

**ተጨነቀ፡ ተሣቀየም፡ አፉንም አልከፈተም፥ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፡ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ** ተጎተተ፡... **አፉንም** አልከፈተም።

**በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፥ ትውልዱን ማን ይናገራል**? **ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ፥** እና... **ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ሆነ።**

**ከክፋዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፡ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ፥ ግፍን ምንም** አላደረገምና፡ **በአፉም ተንኰል** አልተገኘበትምና።

**እግዚአብሔርም ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፥ ለኃዘንም** ሰጠው፥ **ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ፡ ዘሩን ያያል፡ ዕድሜው**ም **ይረዝማል፡ የእግዚአብሔርም ፈቃድ** በእጁ **ይከናወናል።**

**ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያ—ያያል፡ ደስም ይለዋል፥ ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥** ኃጢአታቸውን **ይሸከማልና።**

**ስለዚህም እርሱ ከታላላቆች** ጋር **እድል ፈንታን ይካፈላል፡ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፥ ነፍሱን... ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፥ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን** ኃጢአት **ተሸከመ፡ ስለ ዓመፀኞችም** ማለደ።

33 አጠር እንዳለው ኃይለ ቃል፡ ይህንን ብቻ ልናገር እወዳለሁ። ከዚህም ላይ አንድ ኃይለ ቃል መውሰድ እወዳለሁ፡ እርሱም፥ **የታወቀ የእግዚአብሔር አውራው ሰራ** የሚል ነው።

34 አሁን፡ ይህ የሥራዎቹ አውራ መርጦ ለማውጣት የሚያስችል፡ ለማንበብ የተገባ ቃ—ቃ—ቃል ነው። ሰንመለከትው ግን፡ እንደምናሰበው ከሆነ፡ ከሥራዎቹ አውራ ውጭ ሌላ ማንኛውም ነገር ሊሆን ይችላል፡ ምክንያቱም፡ “ፊታችንን ከእሱ ሰወርን፡ እንወደው ዘንድ ደም ግባት አልነበረውም” ተብሎ ተጽፏል። በብዙ ጊዜያትም፡ እኛ አውራ ብለን የምንጠራውን፡ እግዚአብሔር ምንም ጉዳይ ላይኖረው ይችላል። ምክንያቱም፡ የሰው ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነው፡ የእግዚአብሔር ሞኝነት ግን ከሰው ጥበብ ሁሉ ይልቅ እጅግ ጥበበኛ ነው።

35 እዚህም ውሰጥ፡ እግዚአብሔር የአንድን ነገር ምሰል እንደሰጠን እናያለን። ከእኛ አንዳንዶቻችን አብረን የምንሰበሰብበት፡ የመጨረሻው ጊዜ ሊሆን እንደሚችል ሰለተረዳሁ ይህንን ምሰል በፊታችን ለማምጣት መሞከር እፈልጋለሁ። አሁን እንዳለንበት ዳግመኛ እርሰ በእርሳችን ላንተያይ እንችላለን። ሰለዚህ፡ ለዚህ ዓላማ ከተሰበሰብን፡ ለመታየት ወይም ለመሰማት አይደለም...

36 ነገር ግን ዛሬ ማታ ያንን ድንቅ ማዕድን በጠረጴዛው ላይ እንዳቀረብን አካላዊ ሰውነታችንን እንደመገብን ሁሉ፡ እርሰ በርሳችንም ኅብረት አድርገናል፡ አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ከተሰወረው መናው፡ ነፍሳችንን እንዲመግብ እንወዳለን። ከእርሱ ምግብ እንዲበሉ የተፈቀደላቸው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለሚገቡት ካህናት ብቻ ነው።

37 ዛሬ ማታም፡ የሥጋው—ጥብሳችንን፡ ካሰተዋልን፡ ባገለገልኩባቸው ቦታዎች ሁሉ፡ እስካሁን ድረሰ እንደ ዛሬ ማታው ዓይነት—ግብዣ አግኝቼ አላውቅም፡ ዛሬ ማታ እንዳቀረቡት ዓይነት ጥሩ የሥጋ ጥብሰ፡ በልቼ አላውቅም። አሁን፡ እያችሁ፡ ለመኖር ከፈለግን፡ ይህን መብላት ነበረብን፡ በዚህ የኅብረት ጊዜ ደሰ እንዲለን እንዲሁም አካላዊ ሕይወታችንን ለማቆየት፡ የሆነ ነገር መሞት ነበረበት።

38 በቅርቡ፡ ሥጋ ከማይበላ ሰው ጋር እየተነጋገርኩ ነበር፡ እርሱም፡ “እንግዲህ፡ እ—እኔ ከአንተ ጋር አልሰማማም” አለኝ። እናም፡ ለብቻዬ ሊያገኘኝ እንደፈለገ የሚገልጽ፡ ደብዳቤ—ሰጠኝ። “ወንድም ብራንሃም፡ ሁልጊዜ እንደ ቅዱስ ሰው እቆጥርሃለሁ፡” አለ። “ነገር ግን፡ ለቁርስ የአሳማ ሥጋ እና እንቁላል በልቻለሁ ሰትል ሰሰማ፡ ያ—ያ ቅር አሰኘኝ፡” አለ።

39 ሆኖም፡ እኔ፡ በዚያው መንገድ መቀጠል ሰላልፈለግኩ የተሰናከለበትን ነገር አላነሳሁለትም። አሁን፡ ያ እሱ የሚያምንበት መንገድ ነው። ሆኖም እኔም፡ “እንግዲህ፡ ጌታዬ፡ ካልበላሁ፡ መኖር አልችልም” አልኩት።

40 እሱም፡ “ነገር ግን፡ እየህ፡ እሳማን ትገድላለህ፡ እንዲሁም—እንዲሁም ዶሮን ታርዳለህ” አለ።

41 እኔም፡ “ጌታዬ፡ የምንኖረው በሞተ አካል ብቻ ነው። ምንም ብትበላ አይገደኝም። አትክልቶችን ትበላቸዋለህ። ትበላለህ። ዳቦን ስትበላ፡ ስንዴው ይሞታል። በቆሎን ስተበላ፡ በቆሎው ይሞታል። አተር ስትበላም፡ አተሩ ይሞታል።”

42 የምትበላውን ሁሉ፡ በአካል መኖር የምትችለው አንድ ነገር ሞቶ መኖር ስለምትችል ብቻ ነው። አሁን፡ ምንም ብታደርጉ፡ ወተት እንኳን ብትጠጡ፡ ባክቴሪያው፡ ምንም ይሁን ምን፡ መኖር ያለባችሁ በሞተ አካል ነው። ያም የሚያሳየው፡ ይህንን የተፈጥሮ ሕይወት መኖር ካለብን፡ መኖር የምንችለው በሞተ አካል ብቻ ነው፡ እኛ ለዘላለም እንድንኖርም የሆነ ነገር መሞት ነበረበት። እግዚአብሔር ቤዛ አድርጎ ለእኛ የሰጠን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው።

43 አሁን፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከጴንጤቆስጤ ሰዎች ጋር በተገናኘሁ ጊዜ፡ እ—ከዚህ ወንዙን ተሻግሬ፡ ወደ አጎራባቹ ግዛት፡ ወደ ካሊፎርኒያ ሄድኩ። ሎስ አንጀለስ ነበርኩ። በታዋቂዋ ሴት አገልጋይ፡ ወይዘሮ ሴምፕል... ኤሚ ሴምፕል ማክፐርሰን ዘመን አልኖርኩም ነበር። ወንድ ልጇን ሮልፍን፡ ጥሩ ክርስቲያን ጨዋ ሰውን አገኘሁት፡ እ—እንዲሁም ባለቤቱን እና ቤተሰቡን። በእርግጠኝነት ተወዳጅ ሰዎች ናቸው፡ እንዲሁም ዶክተር ቲፎርድ እና በኤንጀለስ ቤተመቅደስ ውስጥ ያሉ ብዙዎቹ ሠራተኞች አገኘሁ። ከጥቂት ዓመታት በፊትም የጴንጤቆስጤን ኢዮቤልዩ፡ የሃምሳኛ-ዓመት ኢዮቤልዩን፡ እዚያ ሰብኬያለሁ፡ በእርግጠኝነትም ድንቅ ጊዜ አሳልፌያለሁ።

44 ስለዚህ በልቧ ያለውን ለማቅረብ አቅሟ የፈቀደውን ያህል በመሞከሯ፡ ላሳየችው መልካም እርእያ፡ ለዚህች ሴት አክብሮት—ለመስጠት፡ ፎረስት ላውን ወደሚገኘው መቃብሯ ሄድኩ። ቆቤን አውልቄ በዚያ እንደቆምኩ፡ እንዲሁም—እንዲሁም ራሴን አጎንብሼ ለዚህች ታማኝ አገልጋይ የከበረ ሕይወት እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ ሳለ፡ አብረውኝ ከነበሩት አባላት፡ ማለትም ከአገልጋዮች ቡድን፡ ፎረሰት ላውንን ሁሉ ዞሬ... እንድጎበኝ መጎብኘት እፈልግ እንደሆነ ጠየቁኝ። በሬሳ ክፍሉ፡ ወይም እናንተ በምትሉት ሰፍራ ውስጥ ስመለከት፡ ልዩ ልዩ ንድፎችን፡ እንዲሁም የጌታን እራት ተመለከትኩ፡ ቆየሁም። ከእናንተ መካከል ብዙዎቻችሁ፡ የመጨረሻውን እራት አስተውላችኋል፡ መብራት ሲያበሩበት፡ ስለ እርሱ ታሪክ ሰምታችኋል።

45 ነገር ግን እዚያ ካየኋቸው በጣም አስደናቂ ነገሮች አንዱ፡ በበሩ ስትገቡ፡ በምስራቅ በኩል ይመስለኛል። በዚያ የቆመ የ—ሙሴ ሐውልት ነበር፡ ያም በሚካኤል አንጄሎ የህይወት ዘመን ስራ ቁንጮው፡ ይመስለኛል፡ ቀራፂው... የሰውየው ስም ተሳስቼ ሊሆን ይችላል፡ ትክክል ይመስለኛል፡ ያ—ያ... ይህንን የሰራ፡ ወይም፡ የሙሴን ምስል የሰራ ታላቅ ቀራፂ፡ ሚካኤል አንጄሎ ነው። እኛን ይመራን የነበረው፡ አ—አስጎብኚው ሲያብራራም፡ ያ ማይክል አንጄሎ ከጠረባቸው ታላላቅ ድንቅ ሰራዎች ቁንጮ እንደሆነ ተናገረ። እናም ብዙ የሕይወቱን ጊዜና፡ ከባድ ጥረት እንደወሰደበት ተናገረ።

46 ከዚያም፡ በቀኝ ጉልበቱ ላይ ይመስለኛል፡ አንድ ነገር አስተዋልኩ። ሐውልቱ ፍጹምና፡ ልሙጥ ይመሰል ነበር፡ ሙሴም የሕጉን ጽላት በእጁ ይዞ፡ ረጅም ጢሙንም አድርጎ ይታያል። በእርግጥ፡ ያ ማይክል አንጄሎ፡ ሙሴ ምን መምሰል እንዳለበት፡ በአእምሮው የሳለው ምስል ነበር። ምናልባትም

ፎቶግራፍ አይቶ አያውቅ ይሆናል፡ ሆኖም፡ በገዛ አእምሮው፡ ሙሴ ምን መምሰል እንዳለበት ያሰበውን ስሎት ነበር።

47 ታሪኩ እንደሚለውም፡ ሐ—ሐውልቱን ሰርቶ እንደጨረሰ፡ ሁሉንም ወልውሎና አሳምሮ ሲያበቃ፡ ሰራውን ለመመልከት ወደ ኋላ ተመልሶ ቆመ። በጣም ከመመሰጡም የተነሳ፡ ልክ እርሱ ራሱ እስኪመሰል… በአእምሮው የነበረውን፡ በእጁ ሰርቶት ነበር። እጅግ ይመስለው ስለነበር፡ እነዚህን ሁሉ ዓመታት ሲጠብቀው የኖረ ነበርና፡ በመንፈስ ተመስጦ ተወሰደ፡ ጉልበቱ ላይ መታውና በታላቅ ድምጽ፡ "ተናገር" ብሎ ጮኸ! እናም በ—በ—በሙሴ እግርና፡ ጉልበት ላይ የተሰበረ ቦታ አለ፡ እጅግ ስለተመሰጠም፡ ማይክል አንጄሎ በመደሻው የመታበት ቦታ አለ።

48 አያችሁ፡ ከመጀመሪያውም፡ በውስጡ አንድ ነገር ነበረ፡ ሙሴ መምሰል አለበት ብሎ ያሰበውን የአእምሮ ምስል ስሎ ነበር። በፊቱም ሲንጸባረቅ ባየው ጊዜ፡ ልክ በአእምሮው የነበረውን ያንኑ ነገር፡ ሙሴ መምሰል አለበት ብሎ ያሰበውን አየው፥ ያንን ታላቅ የግራናይት ድንጋይ ወሰደ፡ ፍጹም ሆኖ መውጣት ስለነበረበት፡ ከዚህም ከዚያም እየገነጠለ፡ ቅርጽ እያወጣለት፡ ያንን ራእይ እነዚያን ሁሉ ዓመታት በውስጡ ይዞት ቆይቷል። በፊቱም ፍጹም ሆኖ ሲወጣ፡ በአእምሮው የነበረውን ነጸብራቅ አ—አየ። ምስሉን እስኪመታና፡ "ተናገር" ብሎ፡ እስኪጮህ ድረስ፡ ያነሳሳውም ያ ነው! የድካሙ ዓመታት ሁሉ ፍሬ አፍርተዋልና። ታላቅ የእጅ ስራው ተጠናቆ ነበርና።

49 አሁን ይህንን ካየን በኋላ፡ እኔም—እኔም በዚህ ተመስጥኩኝ፡ ምክንያቱም ሳሰበው፡ በእውነት፡ ለእኔ አውራ እንዲሆን፡ ያስቻለው፡ እግር ላይ ያለው ያ ምልክት፡ መሆኑን ስላሰብኩ ነው። ምክንያቱም፡ በቃ፡ ሌላ ተራ ምስል፡ ወይም የሙሴ የሆነ ነገር፡ አንድ ሰው ያሰበው ዓይነት ምስል ቢሆን ኖሮ ምንም አይሆንም ነበር። ሆኖም፡ ሰራውን ይሰራው የነበረው ሰው፡ እስኪመታው ድረስ እጅግ ረክቶ ነበር። ለእኔም በላዩ ላይ ያለውም ያ ምልክት አውራ አደረገው፡ ምክንያቱም ሙሴ ምን መምሰል እንዳለበት በአእምሮው ስሎት የነበረውን ፍጹም አድርጎ አንጸባርቋልና።

50 ኦህ፡ እዚያ ቆምኩኝ። ያ ለእርሱ ምን ት—ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል፡ ለእኔም የሚኖረውን ትርጉም ለማሰብ፡ ለ—ለጥቂት ደቂቃዎች ገለል ብዬ መሄድ ነበረብኝ። ከዚያም፡ ላናግራችሁ ስለፈለግኩት ስለዚህ ጉዳይ ወደ አእምሮዬ መጣ።

51 አሁን ሃሳባችንን ከማይክል አንጄሎ፡ ወደ ታላቁ ቀራፂ፡ ሁሉን ቻይ ወደ ሆነው አምላክ እንመልስ፡ እርሱም፡ በመጀመሪያው፡ ቀን ወይም የንጋት ጮራ ሳይኖር፡ አቶም ወይም ሞለኪውል ሳይኖር፡ እግዚአብሔር፡ በአእምሮው፡ ሰው፡ ምን መምሰል እንዳለበት፡ ምን መሆን እንዳለበት፡ እንዴትስ መንቀሳቀስ እንዳለበት አሰቦ ነበር። ያም ሰው የእርሱ አካል እንዲሆን ፈለገ፡ "ስለዚህ ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፡ በእግዚአብሔርም አምሳል ሰውን ፈጠረው፡" ኦህ፡ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ ይህንን አውራ ሲፈጥር፡ ሀሳቡን የሚያንጸባርቅ ነገር ነበር።

52 አስታውሱ፡ አንዲት አይነት የዘላለም ሕይወት ብቻ አለች፡ እንዲሁም ስ… ስሞቻችንና ሀሳቦቻችን ሳይቀር ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር ዘንድ ነበሩ።

ምክንያቱም አሁን የዘላለም ሕይወት አለን። ያም ለመሆን፡ የእግዚአብሔር አካል መሆን አለብን። ስለዚህ እኛም ልክ በእርሱ ሀሳብ ውስጥ እንደነበርን መሆን አለብን፡ ምክንያቱም የዘላለም ሕይወት አለን፡ ለዚህም ሕይወት አስቀድመን ተወስነናል። ራእይ ላይ እንደሚለውም፡ “ስሞቻችንም ዓለም ሳይፈጠር በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ተጽፈዋል።” አሁን፡ እግዚአብሔር በሀሳቡ ውስጥ ስላኖረን፡ የዘላለም ሕይወት አለን፡ ምክንያቱም ያኔ እርሱ ተናገረን፡ እኛም ወደ ሕልውና መጣን። ቃልም ደግሞ የተገለጠ ሀሳብ ነው። እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ በሀሳቡ ውስጥ አድርጎን ነበር።

53 አሁን፡ ያንን የመጀመሪያውን ሰው፡ አዳምን በፈጠረው ጊዜ፡ እንዴት ፍጹም ነበር። እግዚአብሔርን ይመስል ነበር። ታላቁ መንፈስ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፡ በምድር ላይ አቅፎ በመፈልፈል ነበር፡ በእርሱ... ወፎች ወጡ፡ ምናልባትም፡ እንዲሁም እንስሳት፡ ልዩ ልዩ ነገሮች፡ አቅፎ ይፈለፍላቸው ወደነበረው አምሳል ይበልጥ እየተጠጉ መጡ። በመጨረሻም፡ አቅፎ ይፈለፍላቸው የነበረው፡ ማለትም እግዚአብሔርን የሚመስል ዓይነት ዝርያ፡ እስኪወጣ ድረስ ቀጠለ። እግዚአብሔር፡ ማለቴ፡ ሰው በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ። ከዚያም፡ ልክ ማይክል አንጀሎ ታላቁ የሕይወት ስራውን፡ እና ታላላቅ ቅርጻቅርጾቹን እንዳስቀመጣቸው፡ በታላቅ ገነቱ ውስጥ አኖረው፡ እግዚአብሔር ያንን ታላቅ የእጅ ስራውን በኤደን ገነት ውስጥ አኖረው፡ ረዳትም አደረገለት። ይህ ለእግዚአብሔር፡ እረፍት እስኪሰማው ድረስ የሆነ ፍ—ፍ—ፍጹም እርካታ ነበር። እረፍት ላይ ብቻ ነበር። ስራው ተጠናቆ ነበር።

ከዚያም ስለ ጠላት የሚናገረው፡ አሳዛኝ ታሪክ ይመጣል።

54 አሁን ልብ በሉ። በአእምሮአችሁ እንድትይዙት የምፈልጋችሁ ይህ አንዱ ነገር፡ እግዚአብሔር ለዚህ ሰው ጥበቃ አድርጎለት እንደነበር ነው። አደረገለት... በቃሉ ውስጥ አጥሮ ጠበቀው፡ ምክንያቱም ምን ማድረግ እንደሚችሉና፡ ምን ማድረግ እንደማይችሉ ነግሯቸዋልና።

55 እኛም ዛሬ የተመሰረትንበት ያው መሠረት ነው፡ ምን ማድረግ እንደምንችል፡ ምን ማድረግ እንደማይገባን። የቱንም ያህል ጥሩ ብንሆንም፡ ምንም ያህል ቤተክርስቲያን ብንሄድ፡ ወይም **ይህንን** ብናደርግ፡ ዳግመኛ መወለድ አለብን። አያችሁ? ግድ ነው።

56 እግዚአብሔርም አዳም ምን ማድረግ እንደሚችልና ምን ማድረግ እንደማይችል ነገረው። ከቃሉ ጀርባም አስቀመጠው።

57 ከዚያም፡ ጠላት በማታለል ገባ፡ በሩ ተከፍቶለት ስለነበር፡ በእግዚአብሔር ቃል ግድግዳዎች ውስጥ ሾልኮ ገባ፡ ያንንም ምስል፡ ለኃጢአት አበላሸው። ያም በጣም ከሚያሳዝኑ ታሪኮች አንዱ ነው።

58 ስታስቡት፡ በፈጣሪው መልክ የተፈጠረው ይህ ሰው፡ ያ ቃል ከቶ ሊወድቅ እንደማይችል በማሰብ፡ ከጀርባው የሚቆምበት ግድግዳ የተሰጠው ሰው። የክርስትያን ተስፋ—ይህ ነው። ጋሻውም—ያ ነው። የጦር ዕቃው እርሱ ነው። ዛሬም ዓለቱ ነው፡ ይህም፡ እያንዳንዱ አማኝ፥ ከቃሉ ጀርባ ይቁም።

59 እንግዲህ፡ ጀርባው ከቶ መውጣት የለባችሁም። ያንን ስታደርጉ፡ እራሳችሁ፡ ለጠላት በር ትከፍላላችሁ፡ ይህም፡ “እረ፡ ምን ችግር አለው፡ ትንሽ **ከዚህ**፡ ትንሽም **ከዚያ** ማድረግ ትችያለሽ” በማለት ነው። እግዚአብሔር ኃጢአት

ከተባለ ነገር ሁሉ ራሳችሁን እንድትለዩ ይፈልጋል። ለእርሱ እና ለእርሱ ብቻ፡ ሙሉ በሙሉ የተለያችሁ መሆን አለባችሁ።

60 በሕይወታችሁ ውስጥ ዓላማ አለው፡ እያንዳንዱ ግለሰብ፡ በምድር ላይ ያለ ሌላ ሰው ስፍራችሁን ሊተካ አይችልም። እግዚአብሔር ለእናንተ የያዘላችሁ ነገር አለው። የተፈጠራችሁት እንደዚያ ነው። እንደዚያ የተደረጋችሁት ለዓላማ ነው። እግዚአብሔር በሥራው ሉዓላዊ ነው። እርሱ እንኳ... ነገሮች ይለያያሉ። እኛ ከሌላው፡ እንለያያለን።

61 ይህንኑ በእንስሳት ሕይወት ውስጥም እናስተውላለን። በእንስሳት ሕይወት ውስጥ፡ ብንመለከት፡ እግዚአብሔር እንደ ፈረስ ያለ፡ የሸክም እንስሳን፡ እንደፈጠረ እንረዳለን፡ እሱም—እሱም መሥራት አለበት። ላም ደግሞ መሥዋዕት ናት። እንዲሁ፡ አ—አንበሳ እና ነብር ግን፡ ያለ ምንም ድካም ወይም ያለ ምንም ነገር ጫካውን ይዞራሉ። እንደ ዝሆን ያለ እጅግ ትልቅ እንስሳን ፈጠረ፡ ከዚያም እንደ አይጥ ያለ እጅግ ትንሽ ፍጡርን ፈጠረ። አሁን፡ እግዚአብሔርን ምን ማድረግ እንዳለበት እና እንዴት ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው የሚችል ማን አለ? እርሱ በገዛ መንገዱ ያደርገዋል።

62 ተራራዎችንም ሰራ። በረሃዎችን ሰራ። ባ—ባህሮችንም ሰራ። ሜዳዎችንም ስርቷል። አንዱ ዛፍ፡ ጠንካራ እንጨት፡ ዘንባባ፡ እና—እና ሌላውንም ሰራ። አደረጋቸው።

63 ሰዎችን ልዩ ልዩ አደረጋቸው። ለእያንዳንዳችን፡ ልዩ ልዩ ስፍራዎችን፡ ሰጠን። የዘንባባ ዛፍ ደግሞ ሂኮሪ ሊሆን አይችልም። የሂኮሪ ዛፍ በፍጹም የዘንባባ ዛፍ ሊሆን አይችልም። ማንም ሰው ስፍራችሁን ሊተካ አይችልም፡ እናንተም የሌላውን ስፍራ ለመውሰድ አትሞክሩ። ምክንያቱም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እናንተ ግለሰብ ናችሁ፡ እግዚአብሔርም ለእናንተ የራሱ የሆነ ዓላማ አለው። እንደዚያ የፈጠራችሁ እርሱ ነው። እናንተም፡ "ለምን እንደዚያ አደረገው" ትሉ ይሆናል? እርሱ ሉዓላዊ ነው። እንደዚያ ለመሆኑ የራሱ ምክንያት አለው።

ነገር ግን ሁላችንም በቃሉ ጥበቃ ሥር እንደሆንን ደርሰንበታል።

64 ወደ ሰማይ ስንመለከትም፡ በሰማይ አካላት ላይ ያንኑ እናያለን። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ኮከብ እንኳ ከሌላው ይለያል ይላል። ሳይረስ እና ልዩ ልዩ ኮከቦች አሉ። ማርስ እና ጁፒተር፡ እና ሌሎች የተለያዩ፡ አንዱ ከሌላው የተለያዩ ናቸው። ፀሐይ ከጨረቃ፡ ጨረቃም ከከዋክብት ትለያለች። ደግሞም መላእክት አሉ፡ ለምሳሌ፡ ሱራፌል እና ኪሩቤል፡ እንዲሁም መላእክት እና ታላላቅ መላእክት፡ በ—በየደረጃ አሉ። በሚመጣው አዲስ ዓለም ውስጥ ሳይቀር፡ የምድር ነገሥታት ክብራቸውን ወደ ከተማይቱ ያመጣሉ።

65 እኛም ሁልጊዜም እንደዚያ እንሆናለን። ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር እንደ ሲርስ እና ሮባክ መደብር አይደለም። እርሱ የዓይነቶች አምላክ ነው። አንዱን በአንድ መንገድ፡ ሌላውንም በሌላ መንገድ ይፈጥራል። እኛ ግን እግዚአብሔር በፈጠረን መንገድ እርሱን ማገልገል አለብን፡ እንዲሁም ደስ ሊለን፡ ከቃሉም ጀርባ መቆም አለብን። እግዚአብሔር ያደረገውም እንደዚያ ነው።

66 ዳሩ ግን ያ ጠላት፡ በዚህ፡ የእግዚአብሔር የእጅ ስራ ላይ ሾልኮ በገባ ጊዜ፡ እንዳበላሸው ደርሰንበታል። አሁንም እያደረገ ያለው ልክ ያንኑ ነው።

እሱ በዚህ የእጅ ስራ ውስጥ እሾልኮ እየገባ ነው፡ ያ ጠላት፡ እኛን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ሊያደርገን እየሞከረ ነው። ሆኖም የሰው ልጅ... ታዲያስ፡ የሰው ልጅ እርስ በርሱ እንኳ መስማማት አይችልም፡ ታዲያ ዓለምን ሁሉ ከአንድ ሰው ጋር እንዲስማማ የምናደርገው እንዴት ነው? ልክ ይህን ስታደርጉ...

67 እኛ ከእርሱ ጋር ልንስማማ የሚገባን አንድ አካል አለን፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።” ቃልም እግዚአብሔር ሆኖ ይኖራል፡ ሁልጊዜም እግዚአብሔር ሆኖ ይኖራል፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ነውና። “ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ፡” በእግዚአብሔር ልጅ አካል ውስጥ።

68 አሁን እንደተረዳነው፡ ማለት፡ እኛ በእርሱ ቦታ ብንሆን ኖሮ፡ ይህን ያህል ጊዜና ጥረት፡ አፍስሰንበት ቢሆን ኖሮ፡ ይህን ታላቅ ብልሽት ሲያገኝ፡ ነገሩን በእግራችን ገፍትረን ጥለን እንተወው ነበር፡ እግዚአብሔር ግን፡ እንደዚያ አይደለም፡ ሥራው እንዲጠፋ ፈቃደኛ አልነበረም። ያ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ገጣሚው እንዲህ ማለቱም እያስገርምም፦

ውቅያኖስ ሁሉ ቀለም ቢሆን፡
ሰማይ ሁሉ ብራና ቢሆን፥
የምድር ግንድም ብዕር ቢሆን፡
ሰውም ሁሉ ጸሀፊ ቢሆን፥
የሰማይ አምላክ ፍቅር ቢጻፍ
ውቂያኖሱን ሁሉ ባደረቀው፥
ከአጽናፍ አጽናፍ ቢሆን ጥቅሉ፡
ቢዘረጋም አይዝም ሁሉ።

69 የእግዚአብሔርን ፍቅር እዩት! ሰው ከወደቀ በኋላ እና ሆን ብሎ በሩን ለጠላት ከከፈተለት፡ እንዲሁም ገብቶ ካበላሸውና፡ ሞትን በውስጡ ካስቀመጠበት በኋላ እንኳን፡ እግዚአብሔር ይህ ስራው እንዲሸነፍ አልፈቀደም። ወርዶ ሁሉንም ነገር እንደገና ጀመረ። ያንን ሰው እንደገና ሊያደርገው ወደደ።

70 አዳምን ቃል ኪዳን ገባለትና፡ “**ይህን** አድርግ፡ **ይህን** አታድርግ፥ **ይህም**፡ **ያም** አታድርግ፡ አትንካ፡ አትያዝ፡ አትቅመስ።”

71 ዳሩ ግን እንደገና፡ በጀመረ ጊዜ፡ ከአብርሃም ጋር እንደጀመረ—እንደጀመረ አይተናል። በአብርሃም ላይም፡ ቅድመ ሁኔታ በሌለው ኪዳን ላይ ጀመረው። “ይህን ብታደርግ” በሚል አልነበረም። “እኔ አድርጌዋለሁ። አስቀድሜ አድርጌዋለሁ። አንተን ባርኬሃለሁ፡ አንተንና ዘርህን፡ እንዲሁም፡ ከአንተ በኋላ ሌላውንም” ነበር ያለው። ቅድመ ሁኔታ የሌለው ቃል ኪዳን ነበር የእጅ ስራውን፡ ዳግም በአብርሃም ላይ ሲጀምር፡ የሰጠው ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ በሌለው ኪዳን ነበር። ከዚያም፡ እንዳየነው፡ በአብርሃም ላይ ተመስርቶ፡ ቃል ኪዳኑን፡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሰጠው።

72 ከዚያም ወደ አባቶች ወረደ፡ በብሉይ ኪዳን፡ ወደ ታች ስንወርድ፡ ቀጥለን እንመጣለን። እዚህ ላይ የሰራውን መሰረት አሳየ። አሁን አብርሃም፡ ይስሐቅ፡

ያዕቆብ፡ ዮሴፍ አሉን፥ አራቱ አባቶች።

73 አሁን፡ አብርሃም የእምነት ሰራን፡ እምነትን ይወክላል፡ ምክንያቱም አብርሃም እምነት ነበርና። ታላቅ እምነት ነበረው፡ ምክንያቱም፡ “በእግዚአብሔር ተሰፋ ቃል ባለማመን፡ አልተጠራጠረም።” እኛ እንደምንለው፡ “ነገሮች ሁሉ ገደል አፋፍ ሲደርሱ፡” ሁሉም ነገርም፡ በእርሱ ላይ ሲነሳ፡ አሁንም በእግዚአብሔር ላይ ሙጭጭ ብሎ ነበር።

74 በመቀጠል የተወደደው ልጅ፡ ይስሐቅ ነው፡ እርሱም ፍቅርን ይወክላል፡ ምክንያቱም፡ አብርሃም የእግዚአብሔር ምሳሌ እንደመሆኑ፡ ዘፍጥረት 22 ላይ፡ ይስሐቅ መሥዋዕት ሆኖ እንደቀረበ እናያለን፡ እንጨቱን ተሸክሞ ወደ ተራራው ወጣ፡ እያንዳንዱም ነገር ክርስቶስን ያሳያል፡ አስቀድሞ ጥላ ሆኖ አሳይቶታል። ከዚያም አውራው በግ መጣና በእርሱ ፋንታ መሥዋዕት ሆኖ ቀረበ።

አሁን ያ እምነት፡ ፍቅር ነበር።

75 ከዚያም **ያዕቆብ**፡ ትርጉሙም “ብልጣ ብልጥ” ማለት ነው፡ ያም አታላይ ማለት ነው። ስለዚህ የያዕቆብ ህይወትም በእውነት ጸጋን እንደወከለ እንረዳለን፡ ምክንያቱም፡ የያዕቆብ ነገር፡ ሁሌም የእግዚአብሔር ጸጋ ነበር።

76 ከዚያም ዮሴፍ ይመጣል። በዮሴፍ ላይ ምንም የሚያስነቅፍ ነገር የለም። እርሱ ፍጹም የሆነው ነበረ። በወንድሞቹ መካከል የወጣ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው። ያለ ምክንያትም፡ ተጠላ፡ ተሸጠም። በሁሉም መንገድ፡ ህይወቱ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ጥላ ነበረ። “ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፡ የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም።” ዮሴፍ በወንድሞቹ እንደተጠላ፡ ወደ ጉድጓድ እንደተጣለ፡ እንደሞተም ታሰበ፥ ከዚያም ወጥቶ፡ በፈርዖን ቀኝ ከፍ ከፍ አለ። ከዙፋኑም ሲወጣ፡ መለከት ይነፋ ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ ጉልበት ሁሉ ለእርሱ፡ ለዮሴፍ መንበርከክ ነበረበት።

77 ኢየሱስም ዮሴፍ በተሸጠበት በተመሳሳይ ዋጋ ሊባል በሚችል መልኩ እንደተሸጠ እናውቃለን። ከጉድጓድ ወ—ወጥቶ፡ ወደ ሰማይ ዐረገ፥ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ። ከዚያ ሰፍራ ሲመጣም፡ “መለከት ይነፋል፡ ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፡ ምላሰም ሁሉ ይመሰክርለታል፡” ፍጽምና።

ያ እምነት፡ ፍቅር፡ ጸጋ፡ እና ፍጹምነት ነበር።

78 ከዚያም፡ የዚህ ታላቅ የእጅ የአካል ቅርጽ ሰራ መጣ። ያንን የአካል ሰራ በነቢያት አደረገው። ነቢያቱ ያ የአካል ሰራ ነበሩ።

79 ከዚያም በመጨረሻ የዚህ ታላቅ አካል ራስ መጣ፡ እርሱም ክርስቶስ ራሱ ነበር። ነቢያት ሁሉ ስለ እርሱ ተንብየው ነበር። መሰረቱም ሁሉ ስለ እርሱ አስቀድሞ የተነገረ ነበር ። ከኤደን ገነት ጀምሮ፡ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ፡ “በዘርህና በእባቡ ዘር መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ” ካለበት ጀምሮ። በዚያ እንደጀመረም እየተናል፡ በ—በአባቶች በኩል አድርጎ ወደ ነቢያት መጣ፡ ከዚያም ወጣ። እንደገና የራሱን ነጸብራቅ አየ፡ አንድ ሰው በምድር ላይ፡ ከሴት ማህጸን ሲወለድ፡ ያ የእግዚአብሔር አውራ ነበር። እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። እንደዚያ የሆነበት ምክንያት፡ እርሱ ፍጹም ቃሉ ስለነበር ነው።

80 "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃል ሰጋ ሆነ በእኛም መካከል አደረ።"

81 አሁን በእርሱ ውስጥ ፍጹም የሆነ የሰራው አውራ ተንጸባርቆ እናያለን። እርሱ፡ ልክ እንደ እግዚአብሔር፡ እጅግ ፍጹም ከመሆኑ የተነሳ፡ "የአባቴን ሥራ ባላደርግ፡ አትመኑኝ። እኔን... እኔን ማመን ባትችሉም እንኳ? ማን እንደሆንኩ ስለ እኔ ስለሚመሰክሩ፡ ሥራዎቹን እመኑ፡" አላቸው። ያ ደስ ይለኛል። እያችሁ? እርሱ፡ "እኔን ባታምኑኝም... "

እንዲህም አሉት፡ "አንተ ሰው ሆነህ ሳለህ፡ እራስህን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ታደርጋለህ።"

82 እርሱም፡ "እኔን ማመን ካልቻላችሁ፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እመኑ። የላከኝን ሥራ ባላደርግ፡ እንግዲያውስ እኔን ለማመን መብት የላችሁም።"

83 እንግዲህ ዛሬ፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን፡ ያው ተመሳሳይ ምስክርነት ሊኖረው ይገባል። በዚህ በተሰፋው የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ፡ ሕይወታችን ቃሉ የሚለውን በትክክል የማያሟላና የማይገጥም ከሆነ፡ ዳግመኛ ካልተወለድን ራሳችንን ክርስቲያን ብለን ልንጠራ መብት የለንም። ኢየሱስ በማርቆስ 16 ላይ፡ "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች **ይከተሉአቸዋል**፡" ብሏልና። እያችሁ? "ምናልባት፡ ሊከተላቸው ይችላሉ፡ ምናልባት ይሰጡ ይሆናል" አላለም። ይከተሉአቸዋል። እኛን የፈጠረን ቀራፂ ያ ነው። ተፈልፍላ የወጣችው ቤተክርስቲያን ያች ናት። የክርስቶስ አካል ያች—ያች ናት።

84 አሁን ያ እርሱን ፍጹም አድርጎ እንዳንጸባረቀው ደርሰንበታል። አሁን ቀራፂው፡ ልጁ፡ እግዚአብሔር፡ አማኑኤል በተባለው በዚያ አውራ ውስጥ ቃሉ በድጋሚ እንዲንጸባረቅ አድርጓል። እስቲ አስቡት፡ አንድ ሰው እጅግ ራሱን አሳልፎ ከመስጠቱ የተነሳ፡ እግዚአብሔር ራሱን በዚያ ውስጥ፡ በዚያ አካል ውስጥ እስኪያሳውቅ ድረስ፡ እርሱና እግዚአብሔርም አንድ ሆኑ። "እኔና አባቴ አንድ ነን። አባቴ በእኔ ውስጥ ይኖራል። እኔ ሁልጊዜ አብን ደስ የሚያሰኘውን አደርጋለሁና።"

85 ዛሬ ያለው ክርስቲያን እንደዚህ ያለ ምስክርነት ቢኖረው ኖሮ ምን ይመስል ነበር? እዚሁ ዩማ ውስጥ፡ በመንገዱ ላይ አውራ ትሆኑ ነበር። የልብስ ማጠቢያ ገንዳው ጀርባ ያለሽ ልብስ-አጣቢ ሴት እንኳ ብትሆኚ፡ አሁንም ለእግዚአብሔር አውራው ነሽ። ይህም "ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን፡ አደርጋለሁ" ማለት ስትችዪና፡ ዓለም ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ስ—ስራ በአንቺ ውስጥ ሲንጸባረቅ ማየት ሲችል ነው።

86 በአንድ ወቅት፡ ማቅለጫ ከመኖሩ በፊት፡ ስለ ጥንቱ ወርቅ፡ እንዲህ ተብሎ ይነገራል። ወ... ወርቁን ወስደው ይቀጠቅጡት ነበር፡ ቀጥቃጩ፡ አሪዞና ገና ታዳጊ በነበረችበት የመጀመሪያዎቹ ቀናት ኢንዲያኖች ያንን ያደርጉ ነበር። ወርቅ ቀጥቃጩ የራሱን ምስል በወርቁ ውስጥ እስኪያይ ድረስ ወርቁን ይቀጠቅጡት ነበር። የብረቱን ዝገት፡ እድፉን፡ ቆሻሻውን ሁሉ አውጥተው፡ እስኪቀጠቅጡት ድረስ፡ ቀጥቃጩ፡ ምስሉን በመስታወት እንነስከሚያይ ድረስ ይቀጠቅጠው ነበር።

87 እንግዲህ፡ ወንጌል የሚያደርገው ይህንኑ ነው። ብዙ ሰዎች መገልበጥና መቀጥቀጥ አይወዱም። መቼም፡ ዛሬ ማታ ቤተክርስቲያን የሚያስፈልጋት፡

ጥንታዊው-ዓይነት፡ ዓለምንና የዓለምን ነገሮች የምታወጣበት፡ ጥሩ የመንፈስ ቅዱስ-መቀጥቀጥ ነው። ዛሬ ማታ ጴንጤቆስጤ የሚያስፈልገው ያንን ነው። እንቅስቃሴዎቻችን፡ ዛሬ ማታ የሚያስፈልጋቸው ያንን ነው፡ ወርቅን-አገላብጦ የሚቀጠቅጥ፡ ጥንታዊው-ዓይነት አቀጣቀጥ፡ የዓለም ነገር ሁሉ ከእኛ ተቀጥቅጦ እስኪወጣና፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መልክ እስኪንጸባረቅ ድረስ።

88 ጥቂት ህዝብ ዛሬ ማታ እዚህ ላግኝ፡ ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ የሰጡትንና፡ ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የቀደሱትን። እኔ በዚህች ጥቂት ህዝብ ብዙ ማድረግ እችላለሁ፡ ወይም፡ እግዚአብሔር፡ እናንተ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ከምታደርጉት በላይ፡ እሱ በእግዚአብሔር መንግስት ላይ፡ እዚህ ባሉት ጥቂት ህዝብ እጅግ አብዝቶ ማድረግ ይችላል። አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ እጆቹን አሳልፎ ቢሰጥ፡ እግዚአብሔርም የሚፈልገው ያ ብቻ ነው።

89 ነገር ግን፡ እያችሁ፡ እኛ ዝም ብለን ተኛተን እርሱ **ይህንኛውን** ጎን፡ **ያንኛውን** ጎን እንዲቀጠቅጥ፡ **ይህንን** እንዲያንኳኳ፡ **ያንን** እንዲያንኳኳ፡ **ይህንን** ሀሳብ መትቶ እንዲያሰወግደው፡ እንዲሁም **ያንን** አውጥቶ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መልክ በእኛ ውስጥ እንዲንጸባረቅ መፍቀድ አንፈልግም። በጣም ብዙ ፊልሞችን እናያለን። በጣም ብዙ ቴሌቪዥኖች አሉን። ቤተክርስቲያን በሰዎች ዘንድ ጣዕሟን እስክታጣ ድረስ፡ በጣም ብዙ ሌሎች ዓለማዊ መዝናኛዎች አሉን። ያም መንፈስ ቅዱስ ስለሚወጣና፡ ሌላ ነገር ወደ ውስጥ ስለሚገባ ነው። ያ ትክክል ነው፡ ወዳጆች።

90 እነዚያ ጥንታዊ-ዓይነት የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ እንዴት ሌሊቱን ሙሉ የጸሎት ስብሰባዎችን ያደርጉ እንደነበር፡ ምስክርነቶችን እሰማለሁ። አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ ከአርባ፡ ሃምሳ ዓመታት በፊት፡ ሌሊቱን ሙሉ ይጸልዩ ነበር። ሰዎች በመንገድ ላይ፡ ይጠሏቸው ነበር። ዛሬ ግን፡ እኛ፡ ሁሉም ሰው ትከሻችንን መታ መታ ካላደረገን፡ እንዴ፡ በእኛ ላይ የሆነ ችግር ያለ ይመስለናል። "ሰው ሁሉ መልካም ሲናገርላችሁ ወዮላችሁ።" እርሱ የተናቀ በሰውም የተጠላ ነበር፡ እኛም የእርሱ አምሳል ነን። አሜን።

91 ዛሬ ለእኛ የሚያስፈልገን አንዳንድ እውነተኛ፡ ትክክለኛ የጸሎት ስብሰባዎች ናቸው፡ አንዳንድ ጽዳቶች፡ ከመድረክ ጀምሮ እስከ ጽዳት ሠራተኛው ድረስ፡ ቤቱ ሁሉ፡ በእግዚአብሔር ሊጸዳ፡ ሊቀጠቀጥ፡ የቀጥቃጩን ምስል ሊያንጸባርቅ፡ ወንጌልም በክርስቶስ ትንሣኤ ኃይል ሊሰበክ ያስፈልጋል። ያ ትክክል ነው።

92 ይህ ይዘነው የምንጓዘው ትንሽዬ ማህበራዊ ወንጌል፡ **የዚህንኛው** ትከሻ መታ መታ ማድረግና፡ **ይህንኛውን** ዲያቆን፡ **ያንኛውን** ደግሞ አገልጋይ ማድረግ፡ ወይም እንደዚያ ያለ ሌላ ነገር፡ ሁለቱም ፖለቲካ ነው። በኒቅያ፡ ሮም የተፈጠረው በትክክል ያ አልነበረምን? እኛ ከእነዚያ ነገሮች መራቅ እንፈልጋለን። ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያኖች፡ ጴንጤቆስጤ፡ እና ሁሉም፡ ከዚህ መውጣት አለብን።

93 ፖለቲካ በቤተክርስቲያን ውስጥ ቦታ የለውም። ቤተክርስቲያንን ሊረከባት የሚገባው መንፈስ ቅዱስ እንጂ፡ ማን ምን ይሆናል የሚለው የፖለቲካ ድምጽ አይደለም። "እግዚአብሔርም በቤተክርስቲያን አንዳንዶቹን ሐዋርያት፡ አንዳንዶቹንም ነቢያት፡ አንዳንዶቹንም አስተማሪዎች፡ ወንጌላውያን፡ እና እረኞች አድርጎ ሾመ።" ሰዎች ድምጽ ሰጥተው በዚያ አላስገቧቸውም። በመንፈስ

ቅዱስ ጥሪ፡ በጸሎት ስብሰባዎች፡ እና እጅ በመጫን፡ እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት በመቆየት፡ እግዚአብሔር በዚያ አስቀመጣቸው።

94 ዛሬ፡ ግን፡ ሃይማኖታችንን ማህበራዊ ከማድረጋችን የተነሳ፡ ልክ እንደ ፖለቲካ ራሱ እስኪሆን ድረስ አድርሰነዋል፡ በሁሉም የሐይማኖት ተቋሞቻችን ውስጥ የምንጫወተው ያንን ነው። እኛ... አንዱ በሌላው ላይ ጣት መቀሰር አይችልም። ሁላችንም ጥፋተኞች ነን። በዚያ ውስጥ አንዳንድ እውነተኛ ወንዶችና እውነተኛ ሴቶችን ታገኛላችሁ። ችግሩ ግን፡ እኔ የማስበው፡ ማመን የሚፈልጉትና የእግዚአብሔርን ኃይል—የሚሹት፡ የእውነተኛ ሰዎች ቁጥር እያነሰ ነው። "እንግዲህ፡ **ይህ** ጥሩ ሰው ነው። እሱ ግሩም ሰው ነው፡" በሚል ማህበራዊ ድርጊት ብቻ ብዙዎች ወደ ውስጥ ገብተዋል።

95 ጥሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉን። ጥሩ አብያተ ክርስቲያናትን እነሠራለን፡ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የተሻሉ አብያተ ክርስቲያናት ገንብተናል። ምንም ችግር የለውም። በዚህ ላይ ምንም ተቃውሞ የለኝም። ቤተክርስቲያኗ ስትበለጽግ ማየት እወዳለሁ።

96 ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ በዓለም ነገሮች ከመበለጽግ ይልቅ በጌታ ስልጣን ስትበለጽግ ማየት እመርጣለሁ። ወደ ወንጌል ተመለሱ! ወደ እግዚአብሔር ኃይል ተመለሱ! እንደ መጀመሪያው፡ ወ... ወደ ጴንጤቆስጤ ተመለሱ። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ ችግሩ፡ ያንን መቀጥቀጥ አንፈልገውም።

97 ስለ አንድ ነገር፡ እና ቤተክርስቲያኗ እያደረገች ስላለው ሥነ ምግባር የጎደለው ነገር፡ ወይም—ወይም ስለ አንድ ማህበራዊ ነገር ከተናገራችሁ፡ ወዲያውኑ ያሰወግዷችኋል፡ በሮች ይዘጉባችኋል። መግባት አትችልም፡ ምክንያቱም፡ ሰብሰባ ሰላደረጉ እና ስለሚያግዱህ። ከእንግዲህ አይፈልጓችሁም። እናንተንም፡ "አንተ እብድ ነህ። አእምሮህን ስተሃል" ይሏችኋል። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** እስከሆነ ድረስ ግን፡ ማንም ምንም ይበለኝ ግድ የለውም። ሰውን ለመለወጥ የክርስቶስ ኃይል ያስፈልጋል። ሰውንም ለመጠበቅ የክርስቶስ ኃይል ያስፈልጋል።

98 ኢየሱስ አንድ ጊዜ እንደተናገረው፡ "አበቦቹን ተመልከቱ። እውነት እላችኋለሁ፡ ሰለሞን በክብሩ ሁሉ፡ እንደነዚህ ያህል አላጌጠም።" ሰሎሞን፡ በክብሩ ሁሉ፡ ለማየት አ—አስደናቂ ማራኪ ነበር። ምንም ጥርጥር የለውም። እርሱ ለዓለም ታላቅ ነገር ነበር፡ በእግዚአብሔርም ፊት ታላቅ ሰው ነበር። የሰለሞን ካባ ግን በውስጡ ሕይወት አልነበረውም። ምናልባት ከበግ ጀርባ የተሸለተ፡ የቁሳቁስ ቁራጭ ነበር። አበባው ግን፡ ሕይወት ነበረው።

99 ዛሬ በውስጣችን የሚያስፈልገን የክርስቶስ ሕይወት ነው። የሚያነጻው ያ ነው፥ ውጫዊው፡ የተገለበጠ-አንገትጌ፡ ወይም የተወሰነ የስነ ልቦና ዲግሪ፡ ወይም ሌላ ነገር አይደለም። እኛ መሆን የሚገባንን እንድንሆን የትንሣኤው የክርስቶስ ኃይል ያስፈልጋል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዲገዛ እና በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲነግስ ከመፍቀድ ሌላ ዕቅድ የለውም።

100 ኦህ፡ አምላኬ፡ እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እስኪሆን ድረስ፡ እግዚአብሔርን እጅግ ይመስል ነበር። "እኔና አባቴ አንድ ነን።" ኦህ፡ ማይ! እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ እንዲኖር፡ መላ ሕይወቱም በእግዚአብሔር

የተጠቀለለ እንዲሆን፡ ያ እንዴት ያለ ኑሮ ነበር። ያ አውራ መሆኑ ምንም አያስገርምም!

ሰይጣን ወደ እርሱ መጣ።

101 እግዚአብሔር አውራ አገኘሁ ብሎ ባሰበ ቁጥር፡ ሰይጣን ሁልጊዜ ዘልቆ ይገባ ነበር። በሙሴ ውስጥ ዘልቆ ገባ፡ እርሱም ትእዛዛቱን ሰበረ። ሆኖም ወደዚህኛው ቁንጮ በመጣ ጊዜ ግን፡ እርሱ የእግዚአብሔር የራሱ አውራ ነበር። አሜን። አ—አስቀድሞ ወሰኖት ነበር። ምንም ሊያደርገው አልቻለም። ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ጸና፡ እግዚአብሔርም ተመልክቶት፡ ልክ እንደ ሙሴ በምድረ በዳ ለአርባ ቀናት ሲፈተን አየው። በእርግጥ፡ እነዚያ ሰዎች ሁሉ እርሱን አስቀድመው በጥላ ተርከውታል። ሕጉ ተሰብሮ ነበር። እርሱ በመጣ ጊዜ ግን፡ ሰይጣን፡ ያ ታላቅ ፈታኝ መጥቶ፡ ሊፈትነው በሞከረ ጊዜ፡ በዚያ ያገኘው ሙሴን አልነበረም። አይ፡ ጌታዬ። በዚህኛው ላይ በዘለለበት ጊዜ ክንፎቹን ያቃጠለ አምስት ሺህ ዋት ቮልት ኃይል መታው።

102 እርሱም፡ “ተጽፎአል” አለው። አያችሁ? አዳም አፈገፈገ። ሆኖም፡ ሁለተኛው አዳም፡ ለቤዛነት የመጣው፡ ያ አውራው፡ ኢየሱስ ግን፡ እርሱ ግን፡ “‘ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም’ ተብሎ ተጽፏል፡” አለው። በዚያ አውራ አገኘ። አዎ፡ ጌታዬ። ሌላ ነገርም ተናገረ። እንዲህ አለው፡ “‘እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተን’ ተብሎ ደግሞ ተጽፏል፡ አለው። ከዚህ ራቅ፡ አንተ ሰይጣን።” እርሱ አውራ ነበረ። ምን አደረገ?

103 “ለቤተክርስቲያኔ እነግራለሁ። ቄሶቹ **ይህንና-ያንን-እንዲያደርጉ** አደርጋለሁ። ቢሾፑ **ይህንና-ያንን-ያደርጋሉ፡**” አላለም።

104 እርሱም፡ “ተጽፎአል” አለ። የመጀመሪያውን አዳም የናቀው ያ ነበር፡ እርሱም ወደቀ፡ ሰይጣንም አበላሸው። ዳሩ ግን ምንም ምን ቢያደርግ፡ ይሄኛውን ሊያበላሸው አልቻለም። ስለዚህም፡ እሱ...

105 እግዚአብሔርም፡ “የምወደው ልጄ ይህ ነው። እርሱን ስሙት። ሁሉንም ነገር፡ ሁሉን ነገር ለእርሱ አሳልፌ ሰጥቻለሁ። እናንተ፡ እርሱን ስሙት” አለ። አንድ ነበሩ። ያው አንድ ነበሩ። እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ ኖረ፡ እርሱንም በምድር ላይ አምላክ፡ አማኑኤል፡ አደረገው። እርሱ ፍጹም በግ፡ ኦህ፡ የቤዛነት ፍጹም አውራ ነበር። እንግዲህ፡ ማይክል አንጄሎ እንዳደረገው፡ እግዚአብሔር በእርሱ እጅግ ተደሰቶ ነበር፡ በሕይወቱም እጅግ ተመስጦ ነበር። እንዳየነውም...

106 እዚህ ጋር ጽፌ የያዝኳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ ማርቆስ 9:7 ላይ። በ... መልኩ የተለወጠበት ተራራ ነው። እርሱ በዚያ የመለወጥ ተራራ ላይ ሳለ፡ ሙሴ እንደታየ፡ እንዲሁም ኤልያስ እንደታየ አይተናል።

107 ከዚያም፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ እጅግ ከመመሰጡ የተነሳ፥ እንዲህ እስከማለት ደረሰ፡ “እዚህ ሦስት ዳስ እንሥራ። ከዚህ ውስጥ ሦስት ድርጅቶችን እንሥራ። ሦስት የሐይማኖት ተቋማትን እንሥራ፥ አንዱን ለሙሴ፡ አንዱን ለኤልያስ፡ አንዱንም ለአንተ” አለ።

108 እርሱም ገና ሲናገር፡ ከዚያ ደመና ውስጥ ድምፅ መጣ። ያም ድምፅ፡ “የምወደው ልጄ ይህ ነው። በእርሱ እጅግ ደስ ብሎኛል፡ ስለ እናንተም እቀጠቅጠዋለሁ። እርሱን ስሙት። እርሱ ሊናገር ነው” አለ።

109 “ስለ መተላለፋችን ቈሰለ። ስለ በደላችንም ደቀቀ።” እርሱ በግ ነበር፡ የእግዚአብሔር በግ፡ ፍጹሙ መሥዋዕት። ከቶ ማንም እንደ እርሱ የኖረ የለም፡ ከእርሱም ወዲህ እንደ እርሱ የኖረ ማንም የለም። እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ያዛመደ፡ ፍጹም አውራ ነበር።

110 እግዚአብሔር በመጀመሪያ ቃሉን ሰጠ፡ **ለዚህኛው** የዘመን ክፍል አንድ ድርሻ፡ **ለዚያኛው** ክፍል፡ **ለዚያኛው** ክፍል ብሎ ሰጠ።

111 ዛሬ ሰዎች እጅግ የተታለሉትና የተምታታባቸው እዚህ ላይ ነው። ከአርባ፡ ሃምሳ ዓመታት በፊት በተፈጠረ ነገር ላይ ለመገንባት እየሞከሩ ነው። እኛ… ያ—ያ ለዚያ ዘመን የተሰጠ ነበር።

112 ሙሴ የሄኖክን መልእክት ይዞ—ይዞ ቢመጣ ኖሮ ምን ይጠቅማል? ሙሴ የኖኅን መልእክት ይዞ—ይዞ ቢመጣ ኖሮ ምን ይጠቅማል? ኢየሱስ የሙሴን መልእክት ይዞ—ቢመጣ ኖሮ ምን ይጠቅማል? እያችሁ? ዌስሊ የሉተርን መልእክት ይዞ ቢመጣ ምን ይጠቅማል? ጴንጤቆስጤዎች ከዌስሊ መልእክት ጋር ቢመጡ ምን ይጠቅማል? ምን ማለቴ እንደሆነ ገባችሁ?

113 ሁሉም እዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተከፋፍሎ ተሰጥቷል፡ እኛም ዘመኑንና ሰዓቱን፡ እንዲሁም ለእኛ የተሰጠው ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን። ዛሬም እየወደቅን ያለነው እዚያ ላይ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ሌላውን ነገር ሁሉ እያነበብን ነው። ልንኖርበት የሚገባን ዘመን ይህ ነው። እግዚአብሔር እዚህ ያስቀመጠን ዘመን ይህ ነው። ወደ ቃሉ እንመልከት።

114 እነዚያ ፈሪሳውያን፡ ሰዱቃውያን፡ ሄሮድሳውያን፡ በዚያን ዘመን የነበሩት ልዩ ልዩ ድርጅቶች ነገሩን በሚገባ ስላስተካከሉትና፡ እጅግ ፍጹም አድርገው ስላዋቀሩት፡ ለማምለጥ ምንም መንገድ የሌለ እስኪመስላቸው ድረስ ነበር፡ ኢየሱስን ሳያዩት የቀሩትም፡ በዚህ መንገድ ነው፡ ዳሩ ግን እርሱ በመጣ ጊዜ፡ እርሱ ፍጹም፡ ሁሉም ካሰቡት የተለየ ነበር። በግርግም የተወለደ፡ ትሁት ሰው ነበር፡ እንደ እ… ዲቃላ ልጅ፡ እንዲሁም እነዚህን እነደመሳሰሉ ነገሮች ሁሉ ተቆጠረ።

115 ዳሩ ግን፡ እርሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይመጣል ብሎ በተናገረው መንገድ በትክክል መጣ። እነርሱም ሙሴ በተናገረው ነገር ለምደው ነበር፡ ሙሴም ስለ እርሱ ተናግሮ ነበር። እርሱም፡ “እንግዲህ፡ ሙሴንስ ብታውቁት ኖሮ፡ እኔን ባወቃችሁኝ ነበር። ሙሴ ስለ እኔ ተናግሯልና” አላቸው። አሁንም ሊያዩት አልቻሉም። ማየት እስኪሳናቸው ድረስ፡ በትውፊቶቻቸው ውስጥ እጅግ ተተብትበው ነበር። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ እርሱ የዚያን ዘመን ድርጅቶች ሊያንጸባርቅ አልመጣም። የኑፋቄ ሃይማኖትን ሊያንጸባርቅ አልመጣም።

116 አብን ሊያንጸባርቅ መጣ፡ አብም ቃል ነበረ። አሜን። አሁን መንፈሳዊነት በእውነት ይሰማኛል። የአብን ቃል ሊያንጸባርቅ መጣ። እግዚአብሔር ራሱ በዚያ እንደሚሆን ተናግሮ ነበርና፡ እርሱም እዚያ ነበረ፡ የእግዚአብሔር ፍጹም አውራ ታላቅ የእጅ ስራ። ኦህ፡ ማይ! እርሱ የእርሱ ፍጹም ነጸብራቅ ነበረ። እግዚአብሔር የተናገረውን—የተናገረውን ሁሉ አንጸባርቋል። አዳም ስለ እርሱ

የተናገረውን እንጸባርቋል። ነቢያት ሁሉ የተናገሩትን፡ አባቶች ሁሉ የተናገሩትን አንጸባርቋል። ስለ እርሱ የተነገረው ነገር ሁሉ፡ እርሱ የቃሉ ፍጻሜ ነበረ። ጥላዎች ሁሉ በእርሱ ተፈጽመዋል። አዎ። የአዲስ ኪዳን ይሖዋ ሆነ። እርሱ የብሉይ ኪዳን ይሖዋ ነበረ። በእሳት ዓምድ ውስጥ የነበረው፡ "ያ ቃል፡" "ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።" የብሉይ ኪዳን ይሖዋ የአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ሆነ። እርሱ የእግዚአብሔር ፍጹም ነጸብራቅ ነበረ።

117 ኦህ፡ በጴንጤቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ የነበረችውን ያቺን የመጀመሪያይቱን ቤተክርስቲያን፡ የዛሬይቱ ቤተክርስቲያን ማንጸባረቅ ብትችል ኖሮ! የዛሬው ክርስቲያን ማንጸባረቅ ቢችል ኖሮ! እነርሱ ከነበሩት ጋር ሲነጻጸር፡ እኛ የተዳቀለ ስብስብ ነን።

118 ዛሬ ስመጣ፡ እያለፍኩ፡ ወደዚህ ታች ስወርድ፡ እመለከት ነበር፡ ከእነዚህ ትንንሽ ካሳ ግራንዴ፡ ወይም እዚህ ካሉት ትንንሽ ቦታዎች በአንዱ በኩል ስመጣ፡ የ—የጥጥ እርሻ፡ እና ልዩ ልዩ ልምላሜ እንዳለ አስተዋልኩ። ያንን ለማቆየት፡ ውኃ ለመሳብ በዚያ በንፋስ የሚሰሩ፡ የውሃ ፓምፖች ሊኖሯቸው ግድ ነበር። ለምን? የዚያ ስፍራ ተክል አይደለምና። በእርግጠኝነት አይደለም። ዳሩ ግን፡ ያንን ያረጀውን ቁልቋል ተመልከቱ፡ ለአምስት ዓመታት ዝናብ ባይዘንብም እንኳ በሕይወት ይኖራል። ነገር ግን ያንኛውን ለጥቂት ቀናት ውኃ ማጠጣት ብታቆሙ፡ ይሞታል። አያችሁ፡ ኦሪጂናል አይደለምና።

119 እኛም እንዲሁ ነን። እንደ ህጻን መታቀፍ አለብን፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ትልልቅ ክትባቶች መደረግ፡ ትከሻችንን መታ መታ መባል፡ እንዲሁም **ይሄ፡ ያ**፡ ወይም **ሌላው** ተብለን መጠራት አለብን።

120 እንግዲህ፡ እነዚያ የቀድሞ ክርስቲያኖች ቆራጦች ነበሩ። ማን ጀርባቸውን መታ መታ እንዳደረጋቸው ግድ አይሰጣቸውም ነበር። እነርሱ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ እጅግ ከማንጸባረቃቸው የተነሳ፡ በእነዚያ... እንደ መሃይማንና ያልተማሩ እንደሆኑ ተ—ተቆጠሩ። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አልገቡም፡ የኮሌጅ ዲግሪም አልነበራቸውም። "ዳሩ ግን ከኢየሱስ ጋር እንደ ነበሩ አስተዋሉ።" ዛሬ ያሉ ክርስቲያኖች፡ የሚያስፈልጋቸው ያንን ነው፡ ከኢየሱስ ጋር እንደ ነበራችሁ ሊታወቅላችሁ ይገባል። በእናንተ ውስጥ፡ የተለየ የሆነ አንድ ነገር አለ። እንዲህ እንዳልሆነ አውቃለሁ... ያንን መናገር ተወዳጅነት እንደሌለው አውቃለሁ፡ ነገር ግን እኛ ተወዳጅነትን እየፈለግን አይደለም። ክርስቲያኖች ቀላል የሆነን ነገር አይፈልጉም።

121 ከዓመታት በፊት በቤተክርስቲያኔ ውስጥ፡ አንዲት አሮጊት እህት ቆማ እንዲህ ትዘምር ነበር፡

> ወደ ሰማይ መሄድ ይገባኛል ወይ
> በአበባ አልጋ ላይ ወጥቼ፡
> ሌሎች ሽልማቱን ለማሸነፍ
> በደም ባሕር ሲታገሉ?
>
> አይ፡ ለመንገስ መታገል አለብኝ።

122 እናንተ እዚህ ብትሆኑና ሁሉም ነገር በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ቢነሳ፡ በእርሱ ዘመን ብትኖሩ ኖሮ ምን ታደርጉ እንደነበር አስቡት። ወንድሜ፡ እህቴ፡ እየኖራችሁ ያላችሁት እዚያው ነው። ያ ትክክል ነው። እርሱ አሁንም ቃሉ ነው። ዛሬ

እርሱን እንዴት እየረገጡት እንዳሉ ተመልከቱ። ዓለም ጋር፡ እንዴት ሊያደራጁት፡ ሊያዋህዱት፡ እና እንደዚያ ያለውን ነገር ሁሉ ለማድረግ እየሞከሩ እንዳሉ ተመልከቱ። ተለይታችሁ ቁሙ። ለኢየሱስ ክርስቶስ እና ለ—ለቃሉ ያላችሁን አቋም ውሰዱ። ምንም ነገር ያንን እንዲያደናቅፈው አትፍቀዱ። ከእርሱ ጋር ጸንታችሁ ቁሙ።

123 ከዓመታት በፊት፡ እዚህ አሪዞና እና ካሊፎርኒያ ይመጣ እንደነበረው፡ እንደዚያ ያረጀ ቻይናዊ ልብስ አጣቢ ነው። አንድም የእንግሊዝኛ ቃል መጻፍ አይችልም ነበር። እምብዛም አያውቀውም ነበር። ልብሳችሁን ለእርሱ ታመጣላችሁ። ምን እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ? ትንንሽ ወረቀቶች ነበሩት፡ በላዩ ላይ ምንም ያልተጻፈበት። ያንኑ ወረቀት ቀዶ አንዱን ክፍል ይሰጣችኋል። ስትመለሱም፡ ያ ወረቀታችሁ ከእርሱ ወረቀት ጋር በትክክል መገጠም አለበት፡ አለበለዚያ ልብሳችሁን አታገኙም። እንደውም ያ እጅግ የተሻለ ነው። ስምን ልትቀዱ ትችላላችሁ፡ በዚያ ግን ልታታልሉት አትችሉም፡ ምክንያቱም ያ ወረቀት ከእርሱ ወረቀት ጋር በትክክል መግጠም ይኖርበታልና።

124 እግዚአብሔርም ኪዳኑን ያደረገው እንደዚያው ነው። የእኛ ልምምድ ከአንድ የሐይማኖት መግለጫ፡ ከአንድ ዶግማ፡ ከአንድ የቤተክርስቲያን የሐይማኖት ተቋም ጋር ለመገጠም ሳይሆን፡ ከእግዚአብሔር ቃል፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንዲገጥም ነው። በትክክል። ወደ ክርስቶስ ስንመጣ፡ ክርስቶስም የእኔ ናቸው ይለናል። በቀራንዮ ላይ፡ እርሱን ለሁለት ቀድዶታልና። ከፊሉን ከፍ አደረገው፡ በቀኙም አስቀመጠው፡ እርሱም ሥጋው ነው። መንፈሱን ደግሞ፡ ለእርሱ ሙሽራ እንዲያዘጋጅ፡ ወደዚህ መጣ። በክርስቶስ ውስጥ የነበረው ያው ልምምድ በእኛም ውስጥ መሆን አለበት።

125 እርሱ—እርሱ እጅግ ፍጹም ከመሆኑ የተነሳ ቀራፂውን ደስ አሰኘው፡ በቀራንዮም እስኪቀጠቅጠው ድረስ እጅግ ተመሰጠ። ኦህ፡ ማይ! አሁን መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው፡ እርሱን የእግዚአብሔር አውራ ሆኖ አይተነዋል። “እኛ ግን እንደ ተመታ፡ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ፡ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።” በትክክል አውራው ይህ ነው። አንጀሎ የራሱን ሐውልት እንደመታ፡ ያደረገው ያ ነበር…

126 ጥሩ ሕይወትን ብቻ የሚኖር ቢሆን ኖሮ፡ ዛሬ ማህበራዊ ወንጌልን እንደሚሰብኩት ዓይነት ሰዎች በሆነ ነበር፡ “እርሱ ነቢይ ነበር።” እርሱ ነቢይ ነበር፡ ነገር ግን ከነቢይም የሚበልጥ ነበር። እርሱ እግዚአብሔር ነበር። እርሱ አማኑኤል ነበር።

127 አሁንም እርሱን ለእኔ፡ ያንን—ያንን አውራ በትክክል፡ ለእኔና ለእናንተ ያደረገው፡ እግዚአብሔር ስለቀጠቀጠው ነው። በቀራንዮ ላይ ቀጠቀጠው። እርሱ ባይቀጠቀጥ ኖሮ… ምንም ያህል የሞቱትን ቢያስነሳ፡ ምንም ያህል በታላቅነት ቢሰብክ፡ ታላቅ ሕይወቱ ምንም ቢሆን፡ የይገባኛል ጥያቄዎቹ ምንም ቢሆኑ፡ እርሱ እዚያ ተረጋግጧል። እግዚአብሔር፡ እጅግ ደስ ብሎት ስለነበር፡ እግዚአብሔር ስለ ሌሎቹ ሁሉ ሊቀጠቅጠው የሚችለው በምድር ገጽ ላይ የቆመው ብቸኛው ሰው እስኪሆን ድረስ ነበር። ያ ፍጹሙ ፍጹም ስላልሆኑት ተቀጠቀጠ። በአዳም በኩል፡ የወደቀው ፍጥረት ሁሉ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተዋጀ። የእግዚአብሔር አውራ ፈተናውን አልፏል። እንዴት ቻለው?

በቃሉ ነው። “‘ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡’ ተብሎ ተጽፏል።”

128 ኦህ፡ ክርስቲያን ወዳጄ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበስ። በአንዳንድ የሐይማኖት መግለጫ፡ ወይም በምትቆምለት ሌላ ትንሽ ሀሳብ ጀርባ አትቁም። ጌታችን እንዳደረገው፡ ጠላትን ለመዋጋት ስትወጣ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበስ። በክርስቲያኖች ሁሉ መካከል ደካማ የተባለው እንኳ ሰይጣንን በቃሉ ብቻ እንዴት ሊያሸንፈው እንደሚችል አሳየ። ኃይል ነበረው፡ በፈለገው መንገድ ሰይጣንን ሊቀጠቅጠው ይችል ነበር፡ ነገር ግን ያንን አልተጠቀመም። ቃሉን ብቻ ወሰደና በእርሱ አሸነፈው። “ተጽፎአል። ተጽፎአል።” በየቦታው፡ “ተጽፎአል።” ስለዚህ ሰይጣንን በእግዚአብሔር ቃል አሸነፈው።

129 አሁን፡ ያ ፍጹም አውራ ስራ ነበረ፡ እግዚአብሔርም ቀጠቀጠው። እንዴት ያለ ምሳሌ ነበረ! እንዴት ያለ እውነተኛ ነገር! እዚያ ስላለው የ—ሚካኤል አንጀሎ የቅርጻ ቅርጽ ስራ፡ ሙሴ በእግሩ ላይ ስለመመታቱ እናወራለንን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አለ፡ “ይህ ሰው ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ተጎድቶ ነበር። የሰውን ልጅ እንኳ እስካይመስል ድረስ እጅግ ተጎድቶ ነበር። ተገርፎ ነበር። ደቅቆ ነበር። ደም በደም ሆኖ ነበር። ተሰንጥቆ ነበር።” እ… ሊደረግ የሚችለው ነገር ሁሉ። ልክ እንደ አንድ ትልቅ የደምና—የአጥንት ክምር አብረው የሚሄዱ፡ ይመስል ነበር። ወደ ቀራንዮ ሲጎተት፡ ሰብዓዊ ፍጡር እንኳ አይመስልም ነበር። እግዚአብሔር ለእኛ ሲል ቀጠቀጠው። እርሱን ፍጹም አውራ እንዲሆን ያስቻለው ያ ነው።

130 ኦህ፡ ያንን ለእኔ እንዳደረገው በማወቅ፡ ያንን ለእናንተ እንዳደረገው በማወቅ፡ እጅግ እወደዋለሁ። እንዴት—እንዴትስ ልንተካከለው እንችላለን? ማንም ሊተካከለው አይችልም። ማንም ሊተካከለው አይገባውም። እኛ እዚህ ያለ ተስፋ ነበርን። እኛ ያለ እግዚአብሔር ነበርን። እኛ ምንም ዓይነት የቤዛነት መንገድ አልነበረንም። እያንዳንዳችን በሥጋዊ ግንኙነት ተወልደናል፡ ያንንም ዋጋ መክፈል ነበረብን። ዳሩ ግን ያ ፍጹሙ መጣ፡ እጅግ ፍጹም እና እጅግ ደስ የሚያሰኝ ስለነበር፡ እግዚአብሔር ስለ እናንተና ስለ እኔ ቀጠቀጠው።

131 አሁን፡ ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል፡ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የምትባለውን፡ አውራዋ ሙሽራ ለእርሱ ሊቀርጽ እየሞከረ ነው። ትክክል ነው። እግዚአብሔር እንዴት ያደርገዋል? ከቶ በማይለወጠው መንገዱ፡ በቃሉ ያደርገዋል። እግዚአብሔር ስልቱን ከቶ አይለውጥም። ማንም ሰው፡ ትለወጣላችሁ። እናንተ ትለወጣላችሁ። እኔ እለወጣለሁ። ጊዜ ይለወጣል። ዓለም ትለወጣለች። እግዚአብሔር ግን አይለወጥም፡ እርሱ ፍጹም ነው። እርሱ አይለወጥም። እርሱም ማንኛውንም ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ባደረገበት መንገድ፡ ሁልጊዜም በዚያው መንገድ ያደርገዋል።

132 ሰው ንስሐ ስለገባ አንድ ጊዜ አድኖታል። ሰውን ዳግመኛ የሚያድንበት መንገዱም ያ ነው። እምነት ስለነበረው አንድን ሰው ፈውሶታል። ቀጣዩንም በተመሳሳይ መሰረት ላይ ይፈውሰዋል። መንገዱን ከቶ አይለውጥም፡ ምክንያቱም፡ እያችሁ፡ እርሱ ሉዓላዊ እና የዘላለም ነውና። እርሱ ማለቂያ የሌለው፡ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ፡ ሁሉን አዋቂ ነው። እርሱ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ማንም ሰው ጥበብን እንዲሰጠው መጠየቅ እያስፈልገውም። የበለጠ

እስኪማር ድረስ መጠበቅ አያስፈልገውም። አዲስ ዲግሪ አያስፈልገውም። እርሱ ፍጹም ነው። የትኛውም ዲግሪ ቢሆን፡ መጀመሪያ የሰራው ማንኛውም ነገር፡ የመጀመሪያው ውሳኔው ለዘላለም በዚያው ጸንቶ ይኖራል። መቼም ሊለወጥ አይችልም። ኦህ፡ አቤት ደስ ሲለኝ!

133 የመጀመሪያውንም አውራ በፈጠረ ጊዜ፡ ከቃሉ ጀርባ አስቀመጠው። ሁለተኛውን አውራ በፈጠረ ጊዜ ደግሞ፡ እርሱ ራሱ ቃሉ ነበረ። አሜን። እርሱ ቃሉ ነበረ፥ ከቃሉ **ጀርባ** አይደለም። ዳሩ ግን፡ እርሱ ቃሉ ነበረ። እግዚአብሔር ዕቅዱን ከቶ አይለውጥም። የመጀመሪያዋን ቤተክርስቲያኑን በቃሉ ልክ፡ የጀመረበት መንገድ ያ ነው።

134 አሁን፡ እግዚአብሔር፡ ቃሉ፡ በመጀመሪያ፡ እርሱ ከሌላው ሁሉ ነጻ የሆነ ያልተቀላቀለ ነበረ፡ ከሌሎች ነገሮች፡ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ። አሁን፡ ይህን የምለው የተለየ ሰው ለመሆን አይደለም። እግዚአብሔር የመለያየት አራማጅ ነው። ታውቃላችሁ? እናንተ ስለ መቀላቀል ታወራላችሁ? እግዚአብሔር የመለያየት አራማጅ ነው። በእርግጥ እርሱ እንደዚያ ነው። ሕዝቡን ከዓለም ይለያል። የራሱ ሕዝብ የሆነችውን፡ እስራኤልን ለይቷል። ቤተክርስቲያኑን ከዓለም ሊለይ እየሞከረ ነው፡ ቤተክርስቲያን ግን ከዓለም ጋር መቀጠል ትፈልጋለች። ዳሩ ግን ሕዝቡ አሁንም የተለዩ፡ ለእርሱ የተለዩ ናቸው። እርሱ ማነው? ቃሉ።

135 አንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እያለው፡ መንፈስ ቅዱስም ቃሉን ጽፎት ሳለ፡ ያ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ኖሮት እንዴት ቃሉን ሊክድ ይችላል? በእናንተ ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ለእናንተ የተቀመጠለትን የገዛ ቃሉን እንዴት ሊክድ ይችላል? ሊገባኝ አልቻለም። ከቃሉ ጋር መስማማት አለበት። በእናንተ ውስጥ ያለውም መንፈሳችሁ የእያንዳንዱን የእግዚአብሔር ተስፋ በ "አሜን" ካላረጋገጠ፡ የሆነ የተሳሳተ ነገር አለ።

136 ወንድም ፍሬድ ሶትማን ወይም ዛሬ ማታ እዚህ ያለ አንድ ሰው፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡" ብሎ ጠቅሷል። እርሱ ቃሉ ነው። ያ፡ እርግጥ ነው። እርሱ ሁልጊዜ ያው ነው፡ አያችሁ፡ መንፈሳችሁም ያንን በ "አሜን" ማረጋገጥ አለበት።

137 "ኦህ፡ እርሱ፡ በአንድ መንገድ እርሱ ነው።" በሁሉም መንገድ፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።

138 አሁን እግዚአብሔር ለክርስቶስ—ሙሽራን ማዘጋጀት እንደጀመረ ተረድተናል። ስለዚህ... ሙሽራይቱም የእርሱ አካል ስለሆነች፡ ከእርሱ ጋር መታወቅ በእርሱ ውስጥ መሆን አለባት። አሁን፡ ሙሽራይቱ የእርሱ አካል ናት። እርሷ የእርሱ አካል ናት። የዚያ ዘመን ቃል፡ ሙሽራይቱ የዚያ ቃል አካል ትሆናለች፡ እርሱ ክርስቶስ ነውና። አሁን፡ ያንን ታምናላችሁ? እኛ በክርስቶስ ውስጥ መሆን አለብን። በክርስቶስ ውስጥ፡ እኛ የክርስቶስ፡ በክርስቶስ ውስጥ፡ የክርስቶስ አካል መሆን አለብን።

139 እንዲት ሴት ወንድን ስታገባ፡ ወይም ወንድ ሴትን ሲያገባ፡ ያች ሴት ምንድን ናት? ያች ሴት የእርሱ አካል ትሆናለች። ከእንግዲህ ወዲህ ሁለት አይደሉም። አንድ ናቸው።

140 እግዚአብሔርና ክርስቶስ አንድ በሆኑ ጊዜም፡ እነርሱ አንድ ነበሩ። ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር ቃል ነበረ፡ ቃልም ሥጋ ሆነና። ሥጋውና ቃሉ አንድ ሆኑ። ቤተክርስቲያንም የክርስቶስ ሙሽራ በምትሆንበት ጊዜ፡ እርሷና ወንጌሎቹ ያው አንድ ናቸው።

141 ታዲያ፡ እንዴት፡ “የተአምራት ዘመን አልፏል” ልትሉ ትችላላችሁ? ታዲያ፡ እንዴት፡ “እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው አይደለም” ልትሉ ትችላላችሁ? እናንተ የእርሱ አካል ሆናችሁ ሳለ፡ “እነዚያ ነገሮች ለሐዋርያው ወይም ለደቀመዝሙሩ፡ ወይም በሌላ ዘመን ለነበረ ሰው ነው፡” እንዴት ልትሉ ትችላላችሁ?

142 በዚያን ጊዜ፡ እርሱ፡ “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን ከቶ አያልፍም” ባለ ጊዜስ። ራእይ 22ን በተመለከተስ፡ መጽሐፉን ጽፎ በጨረሰ ጊዜ ምን አለ? እንዲህ አለ፡ “ማንም ሰው በዚህ ላይ አንዲት ቃል ቢጨምር፡ ወይም ከእርሱ አንድ ቃል ቢያጎድል፡ ድርሻው ከሕይወት መጽሐፍ ይወሰዳል ብዬ እመሰክራለሁ” አለ።

143 ታዲያ፡ እንዴት አድርገን፡ ወደ መንግሥተ ሰማያት መጥተን፡ “እንግዲህ፡ **ይህንን** አምናለሁ፡ ያንን ግን አላምንም” ማለት እንችላለን? እናንተ የእርሱ አካል ስለሆናችሁ፡ ሙሉው ቃል መሆን አለባችሁ። እግዚአብሔር ዛሬ ቤተክርስቲያኑን እያዘጋጀ ያለው እንደዚያ ነው፡ በሐይማኖት መግለጫ አይደለም። እነርሱም እኛን ወደዚያ ሊያስገድዱን እየሞከሩ ነው፡ ወገኖቼ። እየመጣ እንደሆነ ማየት ትችላላችሁ። የእጅ ጽሑፉ በግድግዳው ላይ ታይቷል። የዓለም ቤተክርስቲያን ለመሆን ብዙ ጊዜ አይፈጅም። እያንዳንዷ ቤተክርስቲያን አንድም ወደዚያ ውስጥ መውደቅ፡ ወይም ሁኔታዎቹን መቃወም ይኖርበታል። እንግዲህ፡ ያንን ለመቃወም ዝግጁ ናችሁ? ነገሩ ልክ ነው ብላችሁ ስላሰባችሁ ብቻ ባታደርጉት ይሻላል።

144 በውስጣችሁ ክርስቶስ ቢኖራችሁ ይሻላል፡ ምክንያቱም ያ ቃል የዘላለም ነውና፡ ያ ቃልም ዳግመኛ የሚያስነሳችሁ እርሱ ነው። እናንተ የዚያ ቃል አካል ትሆናላችሁ። ከቃሉ ጋር ተቆጥራችኋል።

ዛሬ፡ እናንተ፡ “እኔ ክርስቲያን ነኝ” ትላላችሁ።

145 “የየትኛው ሃይማኖት ተቋም አባል ነህ? ” መልካም፡ ያ ከክርስትና ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

146 የሐይማኖት ተቋማትን በመኖራቸው ምንም ችግር የለውም። እኔ ይሄን አልቃወምም። እናንተ ግን፡ እያችሁ፡ ሰዎቹ፡ እንዲሁ ናቸው... ብዙ ሰዎች እኔ የሐይማኖት ተቋማትን እንደማፈርስ፡ እንደምረግጣቸው ይናገራሉ። አላደርግም። አይ፡ ጌታዬ። የሐይማኖት ተቋማቱ፡ በራሳቸው ምንም አይደሉም። ያ ልክ እንደ የሥራ ሰምምነቶች፡ ወይም እንደዚያ ያለ ማንኛውም ነገር ነው። ነገር ግን፡ “**ከእገሌ-እገሌ** ቤተክርስቲያን አባል ስለሆንኩ እኔ ክርስቲያን ነኝ፡” ስትሉ ስለምትጣበቁ፡ ያ ምንም ትርጉም የለውም። እናንተ የክርስቶስ መሆን አለባችሁ፡ ክርስቶስም ቃሉ ነው። ብዙ ጊዜም እነዚያ የሐይማኖት ተቋማት ምስራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ ያህል ከቃሉ የራቁ ናቸው።

147 ሙሽራ ለመሆን፡ ከዚያ ቃል ጋር መቆየት አለባችሁ። በሙሽራይቱ ውስጥ ከሆናችሁ፡ እናንተ በቃሉ ውስጥ ናችሁ፡ ቃሉም በእናንተ ውስጥ ነው።

እግዚአብሔርን በክርስቶስ በኩል ያንጸባረቀው ቃል፡ ያንኑ እግዚአብሔር በእናንተ በኩል ያንጸባርቃል። አሜን። **አሜን** ማለት "ይሁን።" እንደዚያ፡ ይሁን ማለት ነው። እውነት እንደሆነ አምናለሁ። እናንተ ከእርሱ ጋር መቆጠር አለባችሁ።

148 አሁን፡ እኔ እውነተኛ ትክክለኛ አሜሪካዊ የምሆን ከሆነ፡ የዚህች ብሔር እውነተኛ ዜጋ የምሆን ከሆነ፡ ከእርሷ ጋር መታወቅ አለብኝ። ትክክልም ሆነ ስህተት፡ እርሷ የነበረችውን ሁሉ መሆን አለብኝ። ትክክልም ሆነ ስህተት፡ አሁን ያለችውን ሁሉ መሆን አለብኝ፥ ትክክልም ሆነ ስህተት፡ ወደፊት የምትሆነውን ሁሉ መሆን አለብኝ። አሜሪካዊ ከሆንኩ፡ ከዚህ አገር ጋር መታወቅ አለብኝ። ልክ ነው? በክብሯም ሆነ በውርደቷ፡ በነጻነቷ ወይም በችግሯ፡ እርሷ የትኛውንም ብትሆን፡ እኔ የማይሞት ታሪኳን ስሪ መሆን አለብኝ። እንደ አንድ ወገን መቆም አለብኝ። እርሷ የሆነችውን ሁሉ፡ እኔ ነኝ። እርሷ የነበረችውን ሁሉ፡ እኔ ነኝ። ወደፊት የምትሆነውን ሁሉ፡ እኔ ከእርሷ ተካፋይ መሆን አለብኝ። ያ በትክክል ልክ ነው።

149 ለጥቂት ደቂቃዎች ስለዚህ ነገር አስቡበት። ከዚያም፡ ያንን ለመሆን፡ እንደ አሜሪካዊ... አሁን በማጠቃለል ላይ ሳለሁ፡ በእርግጠኝነት እንድታዩት አድርጌ፡ አቀርብላችኋለሁ።

150 አሜሪካዊ ለመሆን፡ እርሷ እስካሁን ካደረገችው ነገር ሁሉ ጋር መታወቅ አለብኝ። ስለዚህ፡ ከ—ከአባቶች ጋር፡ በፕሊማውዝ ሮክ ደረስኩ። ከመንፈሳዊ ተጓዦቹ ጋር በፕሊማውዝ ሮክ ነበርኩ። በዚያ አብሬአቸው ነበርኩ። ይህችን አገር ከአደጋ ለማስጠንቀቅ፡ አንድ ሌሊት፡ ከፖል ሪቪየር ጋር ጋለብኩ። አሜሪካዊ ከሆንኩ፡ መሆን ነበረብኝ።

እናንተም እንዲህ ትሉ ይሆናል፡ "ኧረ፡ ወንድም ብራንሃም!"

151 አንድ ደቂቃ ጠብቁ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በዕብራውያን 7ኛ ምዕራፍ ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ "አስራትን የተቀበለው ሌዊ እንኳ፡ አስራትን ከፍሏል፡ ምክንያቱም አብራሃም መልከጼዴቅን ሲያገኘው በአያቱ ወገብ ውስጥ ነበረና፡" በቅም-ቅም-ቅድመ አያቱ ዘንድ ነበረ፡ ለእርሱም ተቆጠረለት። የልጅ-ልጁ-በወገቡ ውስጥ በነበረ ጊዜ፡ አብርሃም ለመልከጼዴቅ አሥራት ሲከፍል፡ እግዚአብሔር ቆጥሮለታል። ያንን አደረገውን? ያ ትክክል ነው።

152 ይህች አገር የሆነችውን ሁሉ፡ እኔ ነኝ። ትክክል ነው። ስለዚህ፡ በፕሊማውዝ ሮክ ደረስኩ። ከፖል ሪቪየር ጋር ጋለብኩ።

153 የቫሊ ፎርጅን አቋረጥኩ፡ ከጆርጅ ዋሽንግተን ጋር በዚያ በበረዶ በተሸፈነው ወንዝ ላይ ነበርኩ። ምንም ጫማ ሳይኖራቸው፡ ከብሪታንያ ጋር ለመዋጋት ከዘመቱ አሜሪካውያን ወታደሮች አንዱ ነበርኩ። እግሮቼን በጨርቅ በጠቀለልኩበት በዚያች ጠዋት፡ እግሮቼ በብርድ ቀዝቅዘው ነበር። ዋሽንግተን ሌሊቱን ሙሉ ሲጸልይ አድሮ፡ እስከ ወገቡ ድረስ፡ ረጥቦ፡ ከጫካው ሲወጣ አየሁት። ያ ሲሆን እኔ እዚያ ነበርኩ።

154 ተቃውሞው እጅግ በበረታበት ጊዜ፡ ከስቶንዎል ጃክሰን ጋር ቆምኩ። የስሜኑ ጦር ወደዚያ ታች በተላከ ጊዜ፡ እነርሱም፡ "ሠራዊቱ ሁሉ ወደ ኋላ አፈገፍጓል" አሉ።

ያኔ፡ “ጃክሰን የት አለ” ብለው ጠየቁ?

155 “እንደ ድንጋይ ግድግዳ ቆሟል፡” አሉ። እኔ ከእርሱ ጋር እዚያ ቆምኩ፥ ባለ ሰማያዊ-አይን፡ አጭር፡ ትንሽ ሰው።

156 በአንድ ወቅት ጠየቁት፡ “ተቃውሞው ይህን ያህል በበረታ ጊዜ እንዴት ልትቆም ቻልክ? ”

157 እጅግ ትሁት ሰው ነበር፡ ቦቲ ጫማውን፡ **እንደዚህ** እየመታ፡ “ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ እስካላመሰገንኩ ድረስ፡ አንድም የውኃ ጠብታ ወደ አፌ አልወሰድም፡” አለ። ከእርሱ ጋር በእምነት አቋሙ ቆምኩ። ከሰቶንዋል ጃክሰን ጋር ቆምኩ። ያ ትክክል ነው።

158 ቦስተን የሻይ ግብዣ ላይ ነበርኩ። ከዚያ ከብሪታንያ ሻይ የተወሰነውን ወደ ውቅያኖስ እንድንጥል ረዳሁ። አሜሪካዊ ለመሆን፡ ያ መሆን ነበረብኝ። አዎ፡ ጌታዬ። አዎ፡ ጌታዬ። ከቶማስ ጀፈርሰን ጋር፡ የነጻነት አዋጁን ፈረምኩ። ሐምሌ 4፡ 1776 ላይ፡ የነጻነት ደወልን ደወልኩ።

159 ወንድም በወንድሙ ላይ፡ አባትም በልጁ ላይ፡ በተዋጋበት በዚያ አብዮት ውርደት ውስጥ ተቆጥሬያለሁ። በክብሯ ውስጥ እንደተቆጠርኩ ሁሉ፡ በውርደቷም ውስጥ መቆጠር አለብኝ። ያ በትክክል ልክ ነው።

160 እነዚያ ወታደሮች ሁሉ ሕይወታቸውን ባጡ ጊዜ በዌክ አይላንድ ነበርኩ። ያንን ሲያደርጉ አየኋቸው። ዌክ አይላንድን ሲይዙ አየኋቸው። በጓም ላይ ባንዲራውን እንድናነሳ ረዳሁ። በእርግጠኝነት።

161 የነበረችውን ሁሉ፡ እንዲሁም ያደረገችውን ሁሉ፡ አሁን ያለችውን ሁሉ፡ አሜሪካዊ በመሆኔ ሰለምደሰት፡ እኔ የእርሷ አካል እንደሆንኩ በኩራት እናገራለሁ። እናንተስ አይደላችሁምን?

162 ክርስቲያን ለመሆንም፡ ልክ እንደዚሁ መሆን አለብኝ። ሃሌሉያ! አዎ፡ ጌታዬ። እኔ ክርስቲያን ከሆንኩ፡ እንግዲህ ከኖኅ ጋር ወንጌልን ሰብኬያለሁ፡ እየመጣ ስላለው ፍርድም አስጠንቅቄያለሁ። አዎ፡ ጌታዬ። ወደዚያ ወደ ኋላ፡ በዚያ ውስጥ የእርሱ አካል ነበርኩ። የእግዚአብሔር አሠራር አካል ነበርኩ።

163 በሚነደው ቁጥቋጦ ዘንድ ከሙሴ ጋር ነበርኩ። ከሙሴ ጋር ከግብፅ ተባርሬ ወጣሁ። ወደ ምድረ በዳው አብሬ በረርኩ፡ በሚነደው ቁጥቋጦም ዘንድ ከእርሱ ጋር ነበርኩ። ድምፁን ሰማሁ። ክብሩን አየሁ። እዚያ በዚያ ቁጥቋጦ ጀርባ ውስጥ ከሙሴ ጋር ሲነጋገር የነበረውን፡ የእሳት ዓምድ አየሁ።

164 ቀይ ባሕር ሲከፈል በዚያ ከእርሱ ጋር ነበርኩ። የእሳት ዓምድ በሲና ተራራ ላይ ሲያርፍ አየሁ። በምድረ በዳ መና በላሁ፡ ከተመታውም ዓለት ጠጣሁ። ሃሌሉያ! (አሁን ሃምሳ-አምስት ዓመት እንደሆነኝ አይሰማኝም።) አሜን። አዎ፡ ጌታዬ። በዚያ ማዶ በምድረ በዳ ውስጥ፡ ከእነዚያ ዕብራውያን ልጆች ጋር መና በላሁ። ከዚያም ከተመታው ዓለት ጠጣሁ።

165 ኢያሱ የኢያሪኮን ቅጥር ሲመለከት በዚያም የቆመ ሰው ባየ ጊዜ፡ በዚያች ጠዋት ከኢያሱ ጋር ቆምኩ። እርሱ ሰይፉን መዞ ሊፋለመው ሮጠ፡ አለውም፡ “አንተ ከእኛ ወገን ነህን፡ ወይስ ከጠላቶቻችን? ”

166 እርሱም፡ “እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ነኝ” አለው። ኢያሱ ሰይፉን መሬት ላይ ሲጥል አየሁ። በእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ፊት፡ በሰገድኩ ጊዜ ከኢያሱ ጋር ተንበረከክኩ። መለከት ሲነፋ፡ የኢያሪኮ ቅጥሮች ሲወድቁ አየሁ።

167 ኢያሱም፡ “ፀሐይ ሆይ፡ ቁሚ። አንቺም፡ ጨረቃ ሆይ፡ በኤሎን ቆላ ላይ ቁሚ። አትንቀሳቀሱ” ሲል፡ አየሁ። ፀሐይ ስትቆም፡ ጨረቃም ብርሃኗን መስጠት ሳታቋርጥ አየሁ። ያ ሁሉ ሲሆን አየሁ።

168 በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ከዳንኤል ጋር ነበርኩ፥ በእቶን እሳት ውስጥ ከዕብራውያን ልጆች ጋር ነበርኩ።

169 ዓለም ሁሉ በተቃወመው ጊዜ፡ ከኤልያስ ጋር ነበርኩ፡ አክዓብ እና ኤልዛቤሎቻቸው ሁሉ ጸጉራቸውን ቆርጠው እንዲሁም በዘመኑ በነበሩት ነገሮች፡ ማቅለሚያዎቻቸው እና ፓውደሮቻቸው፡ ቤተክርስቲያንን በያዙት ነገሮች ሁሉ መካከል ነበርኩ። ከኤልያስ ጋር ቆምኩ፡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ፡ ንጹህና ጥርት ያለውን መልእክት አወጅኩ። ሃሌሉያ! በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ብቻውን በቆመ ጊዜ ከእርሱ ጋር ቆየሁ። እሳትን ከሰማይ ወደ ታች ሲጠራ አየሁት።

ዳዊት ጎልያድን ሲገድል ከእርሱ ጋር ነበርኩ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

170 እንግዲህ፡ ክርስቲያን ከሆንኩ፡ በዚያ ሁሉ ውስጥ ተቆጥሬያለሁ። የዚያ አካል መሆን አለብኝ። አዎ፡ ጌታዬ።

በዘመኑ ከኢሳይያስ ጋር ትንቢት ተናግሬያለሁ።

171 ርግብ ወደ እርሱ ስትወርድ ሲያይ ከዮሐንስ ጋር በዮርዳኖስ ላይ ነበርኩ። ከዮሐንስ ጋር በዮርዳኖስ ቆሜ ነበር።

172 የታመሙትን ሲፈውስ፥ አልዓዛርን ሲያስነሳ አየሁት፥ ከሞተች በኋላ፡ የኢያኢሮስ ሴት ልጅ ህይወት ወደ ሕይወት ሲመልሳት አየሁት። እኔ ራሴ አየሁት።

173 በሞቱም ከእርሱ ጋር ታወቅሁ። በቀራንዮ ሲሞት አብሬው ሞቼ፡ በትንሣኤውም ኃይል፡ ከእርሱ ጋር በትንሣኤ ጠዋት ተነሳሁ። ዛሬ ማታ ምስክር ነኝ። ከእርሱ ጋር በቀራንዮ ሞቼ፡ በትንሣኤ ተነሳሁ። ሃሌሉያ! የእሱ አካል ለመሆን፡ ከእርሱ ጋር መታወቅ አለብኝ። በሞቱ ከእርሱ ጋር ተቆጥሬአለሁ። በመከራውም ከእርሱ ጋር ተቆጥሬአለሁ። የሐይማኖት ተቋማት እርሱን በተቃወሙት ጊዜ ከእርሱ ጋር ተቆጥሬአለሁ። ከቤተ መቅደስ ሲያባርሩት፡ ሊጥሉትና ሊያስወግዱት ሲሞክሩ፡ እኔ ከእሱ ጋር ተቆጥሬ ነበር። ያኔ ከእርሱ ጋር ነበርኩ። በሞቱ ከእርሱ ጋር ነበርኩ፡ በትንሣኤ ከእርሱ ጋር ተነሳሁ።

174 ወደ ሰገነቱ ሲወጡ ከአንድ መቶ ሀያ ጋር ነበርኩ። አዎን፡ ወዳጄ። ያንን ኃይለኛ የሚነፍስ ነፋስ ከሰማይ ሲወርድ ነበርኩ። በጴንጤቆስጤ ቀን ከቅቡዓኑ ጋር በልሳን ተናገርኩ። ሃሌ ሉያ! ከእርሱ ጋር ተቆጥሬአለሁና። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! በትክክል። በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ፡ ከጴጥሮስ ጋር ሰብኬያለሁ። ኦህ፡ በዚያ አብሬ ሰብኬያለሁ።

175 በተቺዎች ፊት፡ ከጳውሎስ ጋር በአርዮስፋጎስ ሰበክሁ። አዎን፡ ወዳጄ። መሆን ነበረብኝ።

176 ከዮሐንስ ጋር በፍጥሞ ደሴት ነበርኩ። የመምጣቱ ራዕይ አየሁ። እኔ... ሉተርን—አይቼዋለሁ፡ በተሃድሶው ጊዜ አብሬው ነበርኩ።

ከዌስሊ ጋር ነበርኩ።

177 አሁን ደግሞ እዚህ አሪዞና፡ ዩማ ውስጥ ነኝ። ሃሌሉያ! ዛሬ ማታ፡ እዚህ ስታርደሰት ሞቴል ውስጥ፡ ያንኑ ከሚያምን ህዝብ ጋር ተቆጥሬያለሁ። “አሁን ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ አብረን ተቀምጠናል።” ሃሌሉያ! ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ በክብር ምጽአቱን እየጠበቅኩ ነው። ከእርሱ ጋር ተቆጠርን!

እየኖረ፡ ወደደኝ፥ እየሞተ፡ አዳነኝ፥
ተቀብሮ፡ ሐጢአቴን አራቀ፥
ተነሥቶም፡ በነጻ ለዘላለም ጸደቀ፡
አንድ ቀን ይመጣል፡ አቤት—ያቺ ድንቅ ቀን!

178 አሁን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ታውቄአለሁ፥ እዚያ ውጭ መንገድ ላይ ባለ፡ ወይም ከአርባ ዓመት በፊት በነበረ ነገር አይደለም። አሁኑኑ አለኝ፡ የእግዚአብሔር ክብርና ኃይል፡ የኃጢአት ሰርየት። ድውያንን ሲፈውስ፡ የታወሩ አይኖችን ሲከፍት አየዋለሁ፡ ነገሮችን አስቀድሞ ሲናገር፡ የሰዎችን ልብ ሲያነብ አየዋለሁ። በዚህ ዘመን ባለው አገልግሎቱ ውስጥ ከእርሱ ጋር ተቆጥሬያለሁ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! በዚህ በመጨረሻው ዘመን ለሚሆነው ነጻ መውጣት፡ ከእርሱ ጋር ተቆጥሬያለሁ። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ ከምትመጣው ከታላቂቱ ሙሽራ አካል ለመሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

179 ዓለም ምንም ብትል፡ “እብዶች፡ ጅሎች፡ ወይም ብዔልዜቡሎች፡ ወይም መናፍቃን” ሊሉን ይችላሉ፡ መሆን የፈለጉትን ይሁኑ። እኔ አሁንም ከዚያ ህዝብ ጋር መቆጠር እፈልጋለሁ። አሁንም እዚያ ነኝ። እዚያው እቀጥላለሁ። እዚያ ነው የተወለድኩት። እዚያ መቆየት እፈልጋለሁ። ሁልጊዜም እዚያ እኖራለሁ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በዚያ አኑሮኛልና። እኔ ነኝ። ራሴን ከሆሊ-ሮለር ህዝብ ጋር ለመቁጠር፡ ቤተክርስቲያኔን ትቼ ወጣሁ። አንዱ ነኝ። ከእነሱ ጋር ተቆጥሬአለሁ።

“ቢሊ፡ አንተ አብደሃል፡” ይላሉ።

180 ምናልባት አብጄ ይሆናል፡ ሆኖም የክርስቶስ አእምሮ ተቀበልሁ። ቃሉን አገኘሁ፡ ህልውናውን አገኘሁ፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው እንደሆነ አገኘሁ!... ማንም ስለ እሱ ምንም ቢያስብ አይገደኝም። እኔ ይህ ነኝ። መታወቂያዬን ማድረግ ያለብኝ እኔ ነኝ። በእግዚአብሔር ቃል፡ ከእርሱ ጋር ታውቄአለሁ። “ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡” አለ። እኔም በዚህ በመቆጠሬ ደስተኛ ነኝ። አዎን፡ ወዳጄ።

181 ታውቃላችሁ፡ በአንድ ወቅት፡ ያ ሽማግሌ ቫዮሊን ተጫዋች፡ ታሪኩን ሰምታችኋል፡ ያረጀች ቫዮሊን ነበራቸውና፡ ሊሸጡት በጨረታ አቀረቡት፡ ማንም ግን ሊገዛው አልፈለገም። እንዲህም ጠየቁ፡ “አንድ ዶላር ማን ይሰጣል? አንድ ዶላር ተኩል ማን ይሰጣል? ” በመጨረሻም፡ “አንድ፡ ሁለት፡ አንድ ዶላር ተኩል።”

182 በመጨረሻም ጸጉሩ-የሸበተ ያረጀ ሰው ከህዝቡ መሀል ወጣ። ታሪኩን ታውቃላችሁ። እነሳውና፡ “እስቲ ስጡኝ፡” አለ። በቀስቱ ላይ የተወሰነ ሙጫ አደረገበትና፡ ጥቂት ጊዜ መታው። ህዝቡ ማልቀስ ጀመረ። እንባ በፊታቸው ላይ፡ እንደዚህ ይፈስ ጀመር።

183 ያ ሲሆን፡ ጨረታ አቅራቢው እንደገና አነሳና፡ ጠየቀ፡ “አንድ የሚወስድ ማን አለ፡” አለም፡ “በሺ ዶላሮች፡ ሁለት ሺ፡ አምስት ሺ? ”

184 ልዩነቱ ምን ነበር? ባለሞያው፡ እርሱን የሚያውቀው፡ እርሱን የሰራው ሰው፡ በውስጡ ያለውን እንዴት ማውጣት እንዳለበት ያውቅ ነበር።

185 እኛም አብያተ ክርስቲያኖቻችንን ከሐይማኖት መግለጫዎችና ከሐይማኖት ተቋማት ለማውጣት እስካሰብን ድረስ፡ ከቶ አናደርገውም። የሰውን ልጅ በራሱ አምሳል የፈጠረው፡ ለዚያው ዓላማም ለእርሱ ሙሽራን እየገነባ ያለው፡ የሰው ዘር ብልሃተኛው አናጺ፡ የመንፈስ ቅዱስ ቀስቱ ቃሉን በልባችሁ ውስጥ አንድ ጊዜ ይውጋ፡ ምርጡ ምሳሌአችን ያ ይሆንልናል። ምንም ያህል ወደ ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት ብትሄዱ፡ መጽሐፉ ላይም ምንም ያህል ሰሞች ቢኖሩም፡ በዓለም ላይ ካሉ አብያተ ክርስቲያናት፡ የሐይማኖት ተቋማት፡ የሐይማኖት መግለጫዎች፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትና፡ ድርጅቶች ሁሉ ይልቅ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ ነገር ያደርጋል።

186 እርሱ ሙሽራን እያዘጋጀ ነው። አዎ፡ ወዳጄ። አሁን ቅርፊቶቹን እየጠረበ ነው፡ ዓለምን እየቆረጠ ይጥላል። ኦህ፡ ቤተክርስቲያንን-መቀላቀል፡ እና የሐይማኖት መግለጫዎች፡ እና የሐይማኖት ተቋማት፡ እና ዶግማዎች፡ ሁሉም ከቤተክርስቲያን ተቆርጠው መውጣት አለባቸው፥ የይሰሙላ ሃሳቦቻቸው፡ ግዴለሽነታቸው፡ ትምህርቶቻቸውና ነገሮቻቸው። ተመልሳችሁ ኑና ባለሙያው ቀስቱን እንዲያነሳ ፍቀዱለት። ባለሙያው በእጆቹ ያንሳችሁ፡ ቃሉን ይወርውረው፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው” ይበል።

187 “አሜን፡ ጌታ ሆይ። ቅረጸኝ፡ ስራኝ፡ ጌታ ሆይ፡ መሆን ያለብኝ፡ እንድሆን ፍቀድልኝ፡” በሉት። ከዚያ የተለየ ነገር ይሆናል።

188 ከዚያም፡ “እኔ ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ፡ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ” ይላል። አዎ፡ ወዳጄ።

189 እርሱ አሁን እየቆረጣችሁ ነው፡ ወደ ቃሉ ብቻ እየጠረባችሁ ነው፡ የሐይማኖት መግለጫዎችንና ዶግማዎችን እንዲሁም ሁሉንም ነገር፡ ከእናንተ እያራቀ ነው፡ ለልጁ ሙሽራን፡ ሌላ አውራን፡ የቃሉን አካል አድርጎ ሊመልስ እየሞከረ ነው። ቃሉ።

190 ኢየሱስ ቦታውን ሊወስድ አልቻለም። ያኔ በዚያ ቀን በመጽሐፍ ሲያነብ ታስታውሳላችሁ? የትንቢቱን የተወሰነ ክፍል ብቻ አነበበ፡ የቀረውን ለመጨረሻው ዘመን ተወው። ያንን ክፍል መውሰድ ያለብን እኛ ነን።

191 ስለዚህ፡ እያችሁ፡ እንደጠረበው፡ ልጁን እንደጠረበው፡ ሙሽራውንና ሙሽራይቱን እንዳደረገ፡ ቤተክርስቲያንን ሊጠርባት ይፈልጋል። ሙሽራው ለመሆን፡ የእርሱ አካል መሆን አለባችሁ። የሐይማኖት መግለጫው አካል አይደለም፡ የቤተክርስቲያኑ አካል አይደለም፡ የሐይማኖት ተቋሙ አካል

አይደለም፡ ዳሩ ግን የእርሱ አካል መሆን አለባችሁ። ከሌላ ከማንኛውም ዓይነት መዋቅር መጠረብ፡ አይሰራም። ከቃሉ መጠረብ አለባችሁ። ዓለም ከእናንተ ተቆርጦ፡ ቃሉ ብቻ በእናንተ ውስጥ እንዲኖር መተው አለባችሁ።

192 ታላቁ ቀራፂ ቃሉ በሚጠይቀው መሰፈርት መልክ፡ ራሳችሁን እንድትቀረጹ አሳልፋችሁ ለመስጠት ፈቃደኞች በመሆን በእናንተ ላይ እየቆጠረ ነው። "በመጨረሻው ቀን ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ።" ክርስቶስ የታወቀ ሥጋ የሆነው ቃል አውራ ነው። ለሙሽራይቱ አውራ እንድትሆኑ፡ በዚያው ቃል አማካኝነት፡ ራሳችሁን በእርሱ ውስጥ እንድትታወቁ ተጠይቃችኋል።

193 አሁን፡ ወንድሞች ሆይ፡ እግዚአብሔር ያኔ፡ ለዓለም የሚያቀርበው አውራ ነበረው፡ አሁንም ዛሬ አውራ ይፈልጋል። ፈቃደኞች ናችሁን? ዝግጁ ናችሁን፡ ክርስቲያን ወዳጄ? ዓለም ምንም ብትል፡ ሕይወታችሁ ክርስቶስን በትክክል እንደሚያንጸባርቅ በእውነት እርግጠኞች ናችሁን? "እእምሮህን ስተሃል። አብደሃል። ሄደህ ያንን የሆሊ-ሮለር ወገን ተቀላቅለሃል፡" ይላሉ። እናንተ ለዚያ ምንም ትኩረት አትስጡ።

194 በእውነት በትክክል ካልዳናችሁ፡ እና በዚያ አካል ውስጥ ካልሆናችሁ፡ እና የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ውስጥ ሆኖ ራሱን ካላንጸባረቀ፡ እና የክርስቶስ ሕይወት ከእናንተ ውስጥ ካልተንጸባረቀ፥ ወንድሜ፡ እህቴ፡ ያንን ዕድል አትውሰዱት። እኔ እናንተ ምን እንደሆናችሁ፡ ምን ዓይነት ልምምዶች እንዳላችሁ ግድ አይሰጠኝም፡ ያ ቃል በየቀኑ በእናንተ በኩል እንዲንጸባረቅ አድርጉ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሙሽራን እየወሰደ ነውና።

አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

195 ውድ የሰማይ አባት ሆይ፡ ጥልቅ ማስተዋል ባለው ህዝብ ፊት እንዲህ ያለ የኋላ ቀር መንገድ ይዤ ቀርቤያለሁ። የእኔ ትምህርት በቂ-... በቂ አይደለም፡ ጌታ ሆይ። እኔ በመንገዴ ነገሮችን በቆራረጥኩበት መንገድ መረዳት ካልቻሉ፡ ታላቁ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ቃላት በሰዎቹ ልብ ውስጥ እንዲያሰርጽና፡ ምን ማለቴ እንደሆነ እንዲያዩ እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ። በልቤ ውስጥ፡ ግን፡ አንተ እ—እየሞከርክ ያለኸውን አ—እየዋለሁ።

196 አባት ሆይ፡ ሙሽራይቱ የሙሽራው አካል መሆን እንዳለባት፡ አምናለሁ። እርሷ የእርሱ አካል ስለሆነች፡ ከሙሽራው ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለባት። የእርሱ አካል እስክትሆን ድረስ ከቶ፡ ከቶ ሙሽራው ልትሆን አትችልም። ያም እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡ የሚለው የዛሬው ቃል፡ አካል ነው።

197 አንዴ በምድር ውስጥ የኖረችና፡ መሬት ላይ የወደቀች የስንዴ ቅንጣት፡ ወደ መሬት ውስጥ በገባችው ቅንጣት አምሳል ትነሳለች። ጌታ ሆይ፡ በጴንጤቆስጤ ቀንም፡ ታላቂቱ ቤተክርስቲያን ወጣች። ለመጨረሻው ዘመን ሙሽራና ሙሽሪት ለመሆን፡ ሌላ የስንዴ ቅንጣት ወጣች።

198 በእርሱ ስም፡ መውደቋ፡ ለአንድ ሺህ ዓመታት፡ መውደቋ አይተናል። ከኒቅያ ጉባኤ ጀምሮ፡ መሬት ውስጥ እየበሰበሰች ተኝታ ነበር።

199 ተቺዎቹም፡ **ዝምተኛው አምላክ** የሚለውን መጽሐፍ ጻፉ፡ “ያም ትንንሽ ልጆች እንዲሞቱ፡ በአንበሶች እንዲገደሉ፡ እና እንዲቃጠሉ የሚፈቅድ ነው። ግላዲያተሮችም ክርስቲያኖችን ሰማዕት አድርገዋቸዋል፡ በእንጨትም ላይ አቃጥለዋቸዋል።” ያ ሰው መንፈሳዊ ማስተዋል ኖሮት ቢሆን ኖሮ!

200 ያ ስንዴ በመሬት ውስጥ መበስበስ ነበረበት፡ ነገር ግን ዳግመኛ በቅሎ ወጣ፡ ወደ ታች በወረደበት አምሳል ግን አልነበረም። ወደ ታች የወረደው በስንዴ ቅንጣት አምሳል ነበረ፡ ሲወጣ፡ ግን፡ ልክ አሁን እንደሚበቅል አዲስ ስንዴ፡ ጥቂት ቅጠሎች ነበሩት።

201 በመጨረሻም ከሉተር ወደ ዝዊንግሊ፡ እና ከዚያም ወደ ታች፡ እያደገ መጣ፡ በመጨረሻም ወደ ዛላነት ደረሰ። በዌስሊ ዘመን ራሱን ለወጠ። ከቅጠሎቹ ይልቅ ትንሽ በበለጠ ስንዴውን ይመስል ነበር፡ እጅግም ይመስለው ነበር። ዳግመኛም ወደ ራሱ ማንነት እየተመለሰ ነው።

202 ከዚያም እውነተኛውን ዋናውን የሚመስል፡ ቅንጣት፡ ሆኖ ሲመጣ፡ እናያለን። ዝቅ ብላችሁ ቅርፊቱን ወደ ኋላ ብትገልጡት፡ ያ የመጀመሪያው የስንዴ ቅንጣት በውስጡ ምንም ቅንጣት እንደሌለው ታገኛላችሁ፡ ቅርፊት፡ ቅጠል ነው። ጌታ ሆይ፡ ያ ወደ ፊት የወጣው ታላቁ የጴንጤቆስጤ ሪቫይቫል፡ ጌታ ሆይ፡ እንደዚያ መሆን ነበረበት፡ ስንዴው ሲመጣ ሊሸፍነው ይገባልና። የሚሄድበት ቦታ አልነበረውምና።

203 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ተፈጥሮን የፈጠርክ አንተ ስለሆንክ፡ ነገሮችን ሁሉ በተፈጥሮ አሠራር እንደምንወስድ እናውቃለን። በኖኅ ዘመን፥ ከሰብከቱ በኋላ፡ ባጠመቅሃት መንገድ፡ ምድርን ዋጅተሃል፥ ከዚያም ለራስህ ልትቀድሳት፡ የልጅህን ደም በምድር ላይ አንጠበጠብክ፥ በሚመጣውም ታላቅ ዘመንም፡ በእድሳት ዘመን፡ የዓለማዊነትን ነገሮች ሁሉ ለማቃጠል፡ በእሳት ታቃጥላታለህ። በክርስቲያን ላይ እንዳደረግኸው ሁሉ፡ እርሱን እንዳዳንከው፥ እንዳጠመቅከው፥ እንደቀደስከው፥ ከዚያም ዓለምን ከእርሱ ውስጥ በማደስ አሰወግደህ፡ መንፈስ ቅዱስን በውስጡ በማስቀመጥ፡ የራስህ አድርገህ ትወስደዋለህና።

204 ይህ ስንዴ በመጣበት ተመሳሳይ ሂደት ውስጥ እንዳለፈ እናውቃለን። የእያንዳንዱ ተፈጥሮ አሠራር ያው ነው። አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ቅርፊቱ ወደ ዓለማዊነት እያመራ፡ ከቅንጣቱ ሲለይ ሰናይ፡ ኦህ እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚያ ቅንጣቶች እንዲሆኑ ይሁንልን... ቅ—ቅርፊቱ ወደ ኋላ መፈተግ አለበት፡ ይህም ቅንጣቱ በልጁ ፊት መሆን እንዲችል ነው። ጌታ ሆይ፡ የማጨጃ መሳሪያ መምጣት እሰማለሁ። ብዙም አይዘገይም። ከዚያም ታላቁ አሳንሰር ሙሽራይቱን ወደ ክብር፡ ወደ እግዚአብሔር ህልውና ያወጣታል።

205 አባት ሆይ፡ እያንዳንዳችንን እንድትባርክ፡ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ ይህ የእኛ ዕድል እንደሆነ፡ እንድናስታውስ አድርገን። ነገ ሌላ ላይኖረን ይችላል። የኛ ዕድል ዛሬ ነው። “ዛሬ፡ ከዚህ ሁሉ ዘመን በኋላ፡ ድምፁን ብትሰሙ፡ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ።” ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚህን ሰዎች አላውቃቸውም። ከዚህ የጎደለ፡ ማንም ሰው እዚህ ካለ፡ ዛሬ ማታ የእግዚአብሔርን ሙላት እንዲቀበሉና፡ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ይሁንልን። አባት ሆይ፡ ይሁንልን።

206 አሁንም ራሶቻችንን ዝቅ፡ ልቦቻችንንም፡ ዝቅ እናድርግ። ወዳጆች፡ መልእክቴን የምቆራርጥበትን መንገዴን ይቅር በሉኝ። እግዚአብሔር ማለቴ ምን እንደሆነ ብቻ እንዲያሳያችሁ እ—እጸልያለሁ። አሁን፡ ማ... ማንም ሰው ቀና ብሎ እንዲያይ አልፈልግም። ራሳችሁን እንዳጎነበሳችሁ ቆዩ። እኔ ማ... ማንም ብትሆኑ፡ ሕይወታችሁ እርግጠኛ ካልሆነ...

207 አሁንም፡ እያችሁ፡ ከእነዚያ ሂደቶች እያንዳንዳቸው፡ ምን አደረጉ? ወደ ድርጅት ውስጥ ገቡ። ያ ምን አደረገ? መንፈስ ትቶ ወጣ፡ ወደ ሌላም ሄደ። ሉተር ድርጅት እንደሆነ፥ በቀጥታ ወደ ዌስሊ ሄደ። ዌስሊ ድርጅት እንደሆነ፥ በቀጥታ ወደ ጴንጤቆስጤ ሄደ። ጴንጤቆስጤ ድርጅት እንደሆነ፥ ወዴት እየሄደ ነው? ልክ እንደ እሳት ዓምድ፡ እንዲሁ ይገሰግሳል።

208 አንዳንድ ሰዎች፡ "እኔ ጴንጤ ነኝ፡" ይላሉ። ጥሩ ነው። "እኔ ሉተራን ነኝ።" ያ ጥሩ ነው። ምንም ተቃውሞ የለኝም።

209 ዳሩ ግን፡ ወዳጄ፡ ወዳጄ፡ ስንዴው አሁንም ወደ ፊት እየገሰገሰ ነው። ከታላላቆቹ ሪቫይቫሎች አንዱ የእኛ ሆኖ ቆይቷል። ረ—ረዘም ላለ ጊዜ ቆይቷል፡ ሪቫይቫል ሦስት ዓመት ያህል ብቻ እንደሚቆይ ታሪክ ያሳያል። ይሄኛው ለአስራ አምስት ዓመታት፡ ወይም ከዚያ በላይ ቆይቷል፡ ታላላቅ የፈውስ አገልግሎቶች ነበሩ፡ ሆኖም አሁን ቀዝቅዟል። ተመልከቱ! እያንዳንዱ ሪቫይቫል ሁልጊዜ ከእርሱ በኋላ ድርጅትን ያፈራል። ይሄኛው ለምን አላፈራም? እዚህ አካባቢ የተነሱ፡ የኋለኛው ዝናብ የሚባሉ፡ ትንሽ የወንድሞች ስብስብ ነበሩ፡ የትም አልደረሱም፥ ወዲያውኑ ወደቁ። ለምን? የስንዴው ዘመን ነውና፡ ወዳጆች። ስንዴው ነው። በዚያ በመጀመሪያ ወደ መሬት ውስጥ እንደገባው ዓይነት አገልግሎት ዛሬ በምድር ላይ አለ፡ እውነተኛ የጴንጤቆስጤ ልምምድ።

210 አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት እየሆኑ ነው። አንዱ ከሌላው ይበልጥ ትልቅ ሆኖ ለመገንባት፡ እንዲሁም ቀስ በቀስ፡ ድርጅቶች እየሆኑ፡ ብዙ አባላትንና ሌሎችን ነገሮች ለማግኘት እየሞከሩ ነው። አይተነዋል። እኔ የጴንጤቆስጤ ነኝ። እርሱ ወደ ኋላ ሲገነጠል አይተናል። ዳሩ ግን ምን ይሁን? ልጁ—ልጁ ወደ ቅንጣት መድረስ እንዲችል፡ ያንን ማድረግ አለበት። በመጀመሪያ፡ እዚያ ባይኖር ኖሮ፡ በዙሪያው ምንም ቅርፊት ባይኖር ኖሮ፡ የሚሄድበት ስፍራ አይኖረውም ነበር። እግዚአብሔር ቅርፊት አደረገለት፡ እያችሁ፡ ልክ እንደ በቆሎ፡ ልክ እንደ ስንዴ፡ ከእሸቱ እንደሚወጣ እንደማንኛውም ነገር። አሁንም፡ እያችሁ፡ ከዚህ በኋላ የተነሳ ምንም ድርጅት የለም። ለምን? ለድርጅት የሚሆን ተጨማሪ ጊዜ የለምና። መጨረሻው ላይ ነን።

211 እናንተ መሆን በሚገባችሁ ቦታ ላይ በትክክል ካልሆናችሁ፡ እንዲህ ትሉኝ ይሆናል፡ "ወንድም ብራንሃም፡ እግዚአብሔር ለድውያን የምታደርገውን ጸሎትህ የሚሰማ ከሆነ፡ እና ጌታም ለጸሎት መልስ የሚያደርገውን ሰምቻለሁ... " እንዲሁም ዛሬ በዓለም ላይ ያሉ ሌሎች ሰዎች እየጸለዩ እንዳሉ፡ ሰምታችኋል። እናንተም፡ "እ... ያንን ተሞክሮ እንድቀበል፡ ትጸልይልኛለህን፡ ወንድም ብራንሃም? ዳግመኛ ላላይህ እችላለሁና።" እኔ ላላያችሁ እችላለሁ። "ዳሩ ግን እዚያ እንድደርስ ጸልይልኝ። አሁን እዚያ የደረስኩ አይመስለኝምና። ነገር ግን እኔ እዚያ እንድደርስ፡ አንተ እንድትጸልይልኝ እፈልጋለሁ።"

212 አሁን፡ የሁላችሁ ራስ ዝቅ ይበል። እጃችሁን ወደ ላይ አንሱ፡ እሺ? ጌታ ይባርካችሁ፡ ተባረክ፡ አንተንም። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። በዚህ ሕዝብ ውስጥ፡ ምናልባት፡ ሃምሳ፡ ወይም ስባ-አምስት፡ እጆች ተነስተዋል።

213 እንግዲህ፡ ውዱ ኢየሱስ ሆይ፡ አንተ ዳኛ ነህ። እኛ አገልጋዮች ብቻ ነን። እግዚአብሔር ሆይ፡ እጸልያለሁ። እ—እና በፊትህ ሞገስን ካገኘሁ፡ ጸሎቴን መልስ። እያንዳንዱን እጅ ሲነሳ አይተሃልና። በልባቸው ውስጥ ያለውን ታውቃለህ። ለሕይወት እንደተሾሙ እናምናለንና። ሰይጣንም፡ ልክ በአዳም ዘመን እንዳደረገው፡ ያ አውራው እንዳይወጣ ሊከለክል እየሞከረ ነው። ዛሬ ማታ ይከልከል። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይከልክለው፡ እነርሱም ለእግዚአብሔር አውራ ሆነው ይውጡ። ይሁንልን፡ አባት ሆይ።

214 በክርስቶስ ቃል ውስጥ የታወቁ ይሁኑ። እርሱ እንዳለው፡ "ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ... " ያንን የዳግመኛ-ልደት ልምምድ ይቀበሉ። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት፡ የዓለማዊ ነገሮችን ሁሉ መታደስ ይቀበሉ። ከእንግዲህ በኋላ ያንን አይፈልጉም፡ ጌታ ሆይ። ያንን ዓለም ከእነርሱ አጽዳው፡ በህዝብ ፊትም እንደ አውራ ሆነው ይውጡ። በዚህ በመጨረሻው ዘመን እዚህ በገነት-ጊዜ ዘመን ደስተኛ እንድትሆን፡ ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ፡ እጃቸውን ያነሱትን የእነዚህን ወንዶችና እመቤቶች፡ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች፡ አውራ አድርገህ አቅርባቸው። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ።

215 በከተማው ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ይህ ሪቫይቫልን ባርከው። እግዚአብሔር ሆይ፡ በቅርብ ያለ፡ እያንዳንዱ ወንድና ሴት፡ ያንን ሪቫይቫል እንዲጎበኝ እጸልያለሁ። እንዲሁም እያንዳንዳቸው በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ፡ እና ከየቦታው ያሉ ሰዎች ሁሉ እስኪመጡ ድረስ፡ በዚህች ትንሽ ከተማ ውስጥ የጥንቱ-ዓይነት ሪቫይቫል እንዲያንሰራሩ አድርግልን። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። እነዚህን ነገሮች ሰጠን፡ አባት ሆይ፡ በኢየሱስ ስም እነዚህን እንለምናለን። አሜን።

216 እወደዋለሁ። እወደዋለሁ። እናንተስ ትወዱታላችሁ? ታውቃላችሁ፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ "ብዘምር፡ በመንፈስ እዘምራለሁ።" እገረማለሁ። ዘማሪ ከመሆን በጣም የራቅሁ ነኝ። **እወደዋለሁ**፡ የሚለውን ይህን መዝሙር መጀመር ካልቻልን እንኳን፡ እስኪ አንድ ላይ፡ እንሞክረው። የመዝሙሩን ዜማ ትሰጭናለሽ፡ እህቴ? "ቀድሞ ስለወደደኝ።" ይሄን ሰምታችሁታል። ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ እንየው... ከጥንቶቹ መዝሙሮቼ አንዱ ነው። መዝሙሮች መዘመር እወዳለሁ። በጣም ጥሩ።

217 አሁን አንገታችንን ደፍተን ዓይኖቻችንን ጨፍነን እንዘምር፡ አሁን፡ **እወደዋለሁ** እንዘምር።

> እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
> ቀድሞ ስለወደደኝ
> መዳኔንም ገዛው
> በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

218 እንዘምረው። አንድ ቀን ቀስተ ደመና በሰማይ ላይ ይሞላዋል። የመለከት ድምጽ ይሆናል። በክርስቶስ የሞቱት ይነሣሉ። ኦህ፡ እንዴት እንደምንናፍቀው!

> መዳኔንም ገዛው

በቀራንዮ ላይ።

219 እርሱ አውራችን የሚሆንልን ያኔ ነው።

220 አስታውሱ፡ አውራ ሥራዎች ሁሉ፡ ወደ ክብር አዳራሽ ከመግባታቸው በፊት፡ አስቀድመው፡ በተቺዎቻቸው አዳራሽ ውስጥ ማለፍ ይኖርባችኋል። ተቺዎቹም ሊተቹት ይችሉ እንደሆነ ማየት አለባቸው። ዳሩ ግን ተቺዎቹን ከተቋቋማቸው በኋላ ግን፡ ወደ ክብር አዳራሽ ይወሰዳል። የእግዚአብሔር ልጅ በእያንዳንዱ ድርጅትና፡ የሐይማኖት ተቋም ተቺዎች ውስጥ አልፏል፡ ጲላጦስ እንኳ፡ "በእርሱ ላይ ምንም በደል አላገኘሁበትም" እስኪል ድረስ። ይሁዳም፡ "ንጹህ ደም አሳልፌ ሰጥቻለሁ" ብሏል።

221 ከዚያም እግዚአብሔር አስነሳው፡ እርሱም ዛሬ በእግዚአብሔር ቀኝ፡ በታላቁ የክብር አዳራሽ ውስጥ ተቀምጦ፡ አማላጅነትን እያደረገ ነው። እዚያ ከእርሱ ጋር መሆን አትፈልጉምን? የዚያ አካል መሆን አትፈልጉምን? መሆን ትችላላችሁ። እንድትሆኑ ተጋብዛችኋል። ይህንን መዝሙር እየዘመርን ሳለ፡ ለምን አሁን ከእርሱ ጋር አትነጋገሩበትም።

... ቀድሞ ወደደኝ
መዳኔንም ገዛው
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

222 ዳግመኛ ይህንን ስንዘምረው፡ ከእናንተ ማዶ በጠረጴዛው በኩል ያለውን ሰው እጅ እንድትጨብጡ እፈልጋለሁ። "እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ክርስቲያን ወዳጄ። እግዚአብሔር ይባርክህ። ጸልይልኝ፡" በሉ። አሁን ይህንን እንደገና ስንዘምር፡ እያንዳንዳችሁ ያንን አድርጉ።

እወደዋለሁ... (ጸልይልኝ። ጸልይልኝ።)... እወደዋለሁ
ስለ...

223 በጣም ጥሩ፡ እጅ ለእጅ ተጨባበጡና፡ "ጸልይልኝ፡" ተባባሉ። ሁላችሁም ጸልዩልኝ። በዚያ መገኘት፡ በጣም እፈልጋለሁ።

መዳኔንም ገዛው
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

224 አሁን አንገታችንን ደፍተን ዓይኖቻችንን ጨፍነን፡ እጆቻችንን አንስተን ለእርሱ እንዘምር።

እ... (እግዚአብሔር ሆይ!) እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛው
በቀራንዮ ላይ።

እዚያ የተሰቀለውን አውራ ሥራችሁን ተመልከቱ።

225 ታላቁ ቀራፂ ሆይ፡ ሰውን የፈጠረ፡ የቀረጸውና በገዛ መልክህም ያበጀኸው ታላቅ አምላክ፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ እንድትቀበለን፡ እለምንሃለሁ። ይህች ሌሊት የመታሰቢያ ሌሊት ትሁን፡ ለእኛም፡ በእውነት የምትታወስ ትሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ እዚሁ ስታርደሰት ሞቴል ውስጥ፡ ሰዎችን በእግዚአብሔር ልጆች መልክ እንድትቀርጻቸው ይሁንልን። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። ታላቁ ቀራፂ ሆይ፡ ያንን ማድረግ የምትችለው አንተ ብቻ ነህ። ጌታ ሆይ፡ ቃልህ አምጥተህ፡

በመጨረሻው ዘመን ያንተ አውራ ሥራዎች እንሆን ዘንድ፡ እና የክርስቶስ ሙሽራ ተብለን እንድንጠራ፡ በሁላችንም ልብ ውስጥ ቅረጸው። ሌሎች ሰዎች ለእርሱ በመኖር ውስጥ እንዲህ ያለ እውነታና እንዲህ ያለ ደስታ እንዳለ ማየት ይሁንላቸው።

226 ጌታ ሆይ፡ በዚህ ዘመን፡ አብያተ ክርስቲያኖቻችን እንኳ፡ ቅንነታቸውን እያጡ ነው። እነርሱ አ... ሁሉ ነገር፡ ሆሊውድ የሆነ ይመስላል፡ ጌታ ሆይ፡ ምን እየተፈጠረ ነው? ከእውነተኛው ከሚያበራው ነገር ይልቅ ወደ—አንጸባራቂ ነገር ተወሰዱ። ዓለም በዓለማዊ-ነት እንደምታንጸባርቅ እናውቃለን። ሆኖም ወንጌል ግን በፍቅርና በክርስቶስ ያበራል። ጌታ ሆይ፡ ከዓለም አንጸባራቂነት ርቀን፡ ወደ ክርስቶስ ብርሃን እንገባ ዘንድ፡ ይሁንልን።

227 ጌታ ሆይ፡ የአንተ ናቸው። ገዝተሃቸዋል። አንተ... ዛሬ ማታ፡ እጃቸውን አንስተዋል፡ መሆን ይፈልጋሉ። አሁን፡ አባት ሆይ፡ ብ... ብችል ኖሮ፡ አደርገው ነበር፡ ነገር ግን አልችልም። ነገር ግን በአንተ እታመናለሁ። አንተም፡ “ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ አልጥለውም። ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ወደ ፍርድም አይመጣምና” ብለሃል፡ ጌታ ሆይ፡ አሁን አስመሣይ-እምነት ሣይሆን፡ ነገር ግን እምነት ያለው፡ “ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ።” ይሁን፡ አባት ሆይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ያንተ ናቸውና። አሜን።

228 ትወዱታላችሁ ወይ? ድንቅ አይደለም ወይ?

229 ያንን ትንሽ ዜማ፡ ወይም ኮርድ ሰጪን፡ እህቴ፡ **ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው** የሚለውን።

መዘመር ትወዳላችሁ? እጅግ ጊዜ ወሰጄባችኋለሁን?

230 እኔ ማምለክ እወዳለሁ። እናንተስ አትወዱም? እንደዚህ ያለች ትንሽ፡ የሚቆራርጥ መልእክት፡ እኔ እንግዲህ... ታውቃላችሁ፡ መቁረጥ እጠላለሁ፡ ዳሩ ግን፡ እናንተ—አንድን ሚስማር አጥብቆ እንዲይዝ ለማድረግ፡ ጫፉን ታጥፉታላችሁ። ማለቴ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ። አዎ። አሁን ወደ ታች አጥብቃችሁ መምታት አለባችሁ። አያችሁ?

231 ያን ዝማሬ ትወዱታላችሁ? “ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለእኔ።” ይሄን ታውቁታላችሁ?

ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለእኔ፡
መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል ነው አምላኬ፡
አዳንከኝ፡ ጠበቅከኝ ከሀጢያት ከእፍረት፡
ላምልከው ድንቅ ነው፡ ስሙን ከፍ አድርጌ!

የጠፋሁ ነበርኩ፡ አሁን ተገኘሁ፡ ነጻ ከኩነኔ፡
ኢየሱስ ነፃነት ደህንነት ሰጥቶኛል ለእኔ፥
አዳንከኝ፡ ጠበቅከኝ ከሀጢያት ከእፍረት፡
ላምልከው ድንቅ ነው፡ ስሙን ከፍ አድርጌ!

ሁላችሁም!

ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለእኔ፡
መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል ነው አምላኬ፥

ያዳንከኝ፣ የጠበቅከኝ ከሀጢያት ከእፍረቴ፣
ላምልከው ድንቅ ነው፣ ስሙን ከፍ አድርጌ!

232 አሁን "ጌታ ይመስገን!" እንላለን፣ "ጌታ ይመስገን!" እንደነጸችሁ አይሰማችሁም? ጥሩ ስሜት ይሰማችኋል? ጌታን አምልኩት። እርሱ ድንቅ ነው።

233 ዳግመኛ እስክንገናኝ ድረስ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። አሁን አገልግሎቱን ለወንድሜ እሰጠዋለሁ፣ ፕሬዝዳንት።

64-1205 የታወቀ የእግዚአብሔር አውራው ስራ
ስታርዳስት ሞቴል
ዩማ, አሪዞና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰሩ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org